# Major Themes in the Study of Ethiopian Customary Laws

Muradu Abdo ♣

## Abstract

The literature covered in this Article reveals different perspectives. On the one hand, there is the idea that customary law systems should be set aside as they are inimical to national development and unity. On the other hand, there is the view that those customary legal systems which do not offend individual rights shall be given due place owing to their multifaceted benefits while only those customary laws which violate individual rights shall be abolished is gaining importance. The issue of whether customary laws should be given recognition on account of collective identity or because of their instrumental value is not addressed in the researches reviewed. The interface between customary law systems and state legal system is not fully investigated in the existing literature on the subject. There is some research conducted on customary law systems of Ethiopia on the initiative and financial support of the Government at Federal or regional levels. The initiative aims at deploying these researches as inputs for legal and institutional reform, to use them for the benefit of the current generation as well as to preserve, improve and pass them on to the next generation. This article recommends that researches on customary law systems of Ethiopia conducted by anthropologists, social workers, historians and political scientists deserve future review as the current article has not considered them. Those customary legal systems of Ethiopia which are not yet studied or insufficiently studied warrant exploration. Notwithstanding various research initiatives with the financial support of international institutions, there is a need to have government-led and financed study on customary systems of the country. There should be an institution which assumes this responsibility. The extent of recognition given to customary law systems in the Federal Constitution, proclamations and policies should be duly examined; and there should be policy and detailed legal framework regarding customary law systems of the Country.

## Key terms:

Customary laws · Customary legal systems · Law and development · Modernization · Socialist legality · Post-modernism · Sharia law

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v16i2.7

This article is licensed under a Creative Commons Attribution-NonCommercial-NoDerivs **(**CC BY-NC-ND)

♣ Muradu Abdo (PhD), Associate Professor, Addis Ababa University, School of Law
Email: muradu.abdo@aau.edu.et
ORCID: https://orcid.org/0000-0003-3725-3581

**Received**: 22 July 2022 **Accepted**: 15 October 2022

**Suggested citation**:

Muradu Abdo (2022). “Major Themes in the Study of Ethiopian Customary Laws” (Amharic), 16(2) *Mizan Law Review*: 423-454.

ሙራዱ አብዶ (2015 ዓ.ም.)፣ “በኢትዮጵያ ልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶች ላይ የተከናወኑ ምርምሮች ፍተሻ”፣ *ሚዛን የሕግ መጽሔት*፣ ቅጽ 16፣ ቁ. 2፣ ገጽ 423-454

## Contents

1. Introduction

2. 1960s to Mid 1970s

3. Mid 1970s to the late 1980s

4. 1990s to 2021

5. Conclustions and the Way Forward

# በኢትዮጵያ ልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶች ላይ የተከናወኑ ምርምሮች ፍተሻ


## አጽህሮተ ጽሑፍ

በዚህ ጽሑፍ ዳሰሳ የተደረገባቸው ምርምሮች በጥቅሉ ሲታዩ፣ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ለሀገር ልማትና አንድነት ስለማይበጁ መጥፋት አለባቸው የሚለው አስተሳሰብ እየከሰመ መምጣቱን፤ በምትኩ የመብት ጥሰቶችን የማያስከትሉ የልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶች በብዙ መልኩ ጠቃሚ በመሆናቸው ቦታ ሊሰጣቸው እንደሚገባ፣ በአንፃሩም መወገድ ያለባቸው የመብት ጥሰት የሚያደርሱት ብቻ እንደሆኑ የሚገልፀው አስተሳሰብ እየጎላ መምጣቱን፤ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች እውቅና ሊሰጣቸው የሚገባው በመሣሪያነታቸው ነው ወይንስ የማህበረሰብ ማንነት መገለጫ በመሆናቸው የሚለው ጥያቄ በሚገባ አለመጤኑን፤ በልማዳዊ ሕግ ሥርዓትና በመንግሥት ሕግ ሥርዓት መካከል ያለው ተግባራዊ መስተጋብር በቅጡ አለመፈተሹን፤ ለሕግ ማሻሻያ ግብዓት እንዲሆኑ፣ አሁን ያለው ትውልድ እንዲጠቀምባቸው፣ እንዲሁም ለመጪው ትውልድ ተጠብቀው መተላለፍ ይችሉ ዘንድ በመንግሥት አነሳሽነትና የፋይናንስ ድጋፍ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶችን በሚመለከት የተከናወነ የምርምር ሥራ አለመታየቱን የሚያመለክቱ ናቸው። በምክረ-ሐሳብ ረገድ፣ በሥነ-ሰብእ ባለሙያዎች፤ በሶሺያል ዎርከርስ፤ በታሪክና በፖለቲካ ሳይንስ ባለሙያዎች ምርምሮች ላይ ተመሥርተው በልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶች ላይ የተሠሩ ጥናቶች በዚህ ጽሑፍ ያልተሸፈኑ በመሆኑ በቀጣይ ሊፈተሹ ይገባል፤ ያልተጠኑ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች፣ እንዲሁም ተጠንተውም በጥልቀት ያልተሄደባቸው ስላሉ በእነዚህ ላይ ምርምር ሊደረግ ይገባል፤ በተለያዩ በውጭ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ የሚሠሩ ጥናቶች እንደተጠበቁ ሆነው መንግሥት እራሱ የሚመራውና በገንዘብ የሚደግፈው በልማዳዊ ተቋማት ላይ የሚደረግ ምርምር እንዲኖር ያስፈልጋል፤ ይህንንም የሚያከናውን ተቋም ሊኖር ይገባል፤ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፤ በአዋጆችና በፖሊሲዎች ለልማዳዊ ሕግጋት የተሰጠው እውቅና በቅጡ ሊፈተሽ ይገባል፤ የልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶች የሚመለከት ፖሊሲና ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ መቅረጽ ያስፈልጋል የሚሉ የመፍትሔ ሐሳቦችን ይህ ጽሑፍ ያቀርባል።



## ቁልፍ ቃላት

ልማዳዊ ሕጎች፤ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች፣ እውቅና፣ መስተጋብር፣ ሕግ እና ልማት፣ ዘመናዊነት፣ ሶሻሊስታዊ ሕጋዊነት፣ ድህረ-ዘመናዊነት፣ የሸሪዓ ሕግ


## ይዘት


1. መግቢያ
2. እኤአ ከ1960ዎቹ እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ
3. እኤአ ከ1970ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ
4. እኤአ ከ1990ዎቹ እስከ 2021
5. መደምደሚያና ምክረ-ሐሳብ

## 1. መግቢያ

አያሌ የአፍሪካ አገራት እኤአ ከ1960ዎቹ እስከ 1970ዎቹ[1] ልማዳዊና ዘመናዊ የሕግ ሥርዓታቸውን እንዴት አጣጥመው መሄድ እንዳለባቸው ያውጠነጥኑና ይከራከሩ ነበር። ኢትዮጵያ ግን፣ በዚሁ ጊዜ የልማዳዊ ሕግጋቷን በአብዛኛው በመሻር ከምዕራቡ ዓለም ያመጣቻቸውን ሕግጋት ተግባራዊ ለማድረግ እየጣረች ነበር። ይህንንም ጥረቷን ስድስት ዘመናዊ ሕብረ-ሕግጋትን/ መድብለ-ሕግጋትን (law codes) በማወጅ አሳይታለች።[2] እነዚህን ሕግጋት የሚተገብሩ ባለሙያዎችን ለማሠልጠን ይረዳ ዘንድ በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን የሕግ ፋክልቲም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) እኤአ በ1963 መሥርታለች። ከምዕራቡ ዓለም በተለይም ከአሜሪካ የመጡ የሕግ መምህራን የመጀመሪያዎቹ መምህራን ነበሩ።

በእነዚህ ሕግጋት ላይ የሕግ ምርምር እንዲሠራም በንጉሠ ነገሥቱ በራሳቸው የበላይ ጠባቂነት የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት የተጀመረውም እኤአ በ1964 ነበር። በዚህ መጽሔትና በሌሎች ታዋቂ የዓለም አቀፍ የምርምር መጽሔቶች ሕብረ-ሕግጋቱን የማብራራትና ለልማዳዊ ሕግ ምን ያህል ቦታ እንደቸሩ ከነምክንያቶቹ ጭምር ተተንትነዋል። እንዲሁም ሕግጋቱ ወጤታማ እንዳይሆኑ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ተለይተዋል። ሕግጋቱ ወደ ሕዝቡ መዝለቅ አለመዝለቃቸውንም ፈትሸዋል። እኤአ እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ ዓመታት የሀገሪቱ አጠቃላይ ጥረት ልማትና ዘመናዊነትን የምዕራቡን ዓለም ሕግ በመጠቀም ማምጣት ይቻላል በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ነበር።

እኤአ በ1970ዎቹ አጋማሽ ከፈነዳው የኢትዮጵያ አብዮትና ተከትሎት ከመጣው ርዕዮተ-ዓለም ለውጥ ጋር ተያይዞ የተከሰተው ሁኔታ በዚህ የሕግ ሥርዓት የማዘመን ጥረት ላይ ጥላ አጠላበት። ይህም ደርግ እስከ ወደቀበት እኤአ እስከ 1990ዎቹ መጀመሪያ ድረስ ዘልቋል። ይህ ወቅት በተለይ በልማዳዊ ሕግ ሥርዓት ላይ የተሠሩ ምርምሮች ያልታዩበት ነበር።

እኤአ ከ1990ዎቹ ጀምሮ ጀምሮ ለውጦች ተስተውለዋል። በአንድ በኩል በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ሀገሪቱ የሰብአዊ መብቶችን ለማክበር ቃል-ኪዳን ገብታለች። በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ ሕገመንግሥት ሀገሪቱ የሕዝብ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ተቀብላለች። ይህም ሀገሪቱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ውስጥ ሳትገባ የሕግ ብዝሀነትን የሚያመለክተውን የቡድን የራስ ገዝ መብት እስከምን ድረስ ተግባራዊ ማድረግ ትችላለች በሚለው ጭብጥ ምርምሮች እኤአ በ1990ዎቹ ተከናውነዋል። የዓለም አቀፍ ልማት ድርጅቶች ፊታቸውን ወደ ልማዳዊ ሕግ ማዞራቸውን ተከትሎ በጉዳዩ ዙሪያ ምርምር እንዲደረግ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ መጀመራቸው፤ እንዲሁም ደግሞ የመደበኛው ሕግ ሥርዓት ውሱንነት ማለትም የዳኞች ቁጥር ማነስና የተደራሽነቱ እጥረት ግልጽ ሆኗል።

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ እኤአ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ላይ ለሕትመት የበቁ ምርምሮችን በጥቅሉ በመዳሰስ ለፖሊሲና ሕግ ግብዓት የሚሆኑ ሓሳቦችንና ተጨማሪ ጥናት የሚሹ ጭብጦችን መጠቆም ነው። ይህ ጽሁፍ እያንዳንዱ

---

[1] በዚህ ጽሑፍ የተጠቀሱት ዓመተ ምህረቶች የአውሮፓውያን የዘመን ቀመር የተከተሉ ናቸው።

[2] Penal Code (1957); Civil Code (1960); Commercial Code (1960); Maritime Code (1960); Criminal Procedure Code (1961) and Civil Procedure Code (1965).

ምርምር ላይ ጥልቅ ትንተናና ሂስ የመስጠት ዓላማ የሌለው መሆኑን ጸሐፊው ለአንባቢያን ማሳወቅ ይፈልጋል፡፡

በርዕሱ ላይ በተለይም እኤአ ከ1990ዎቹ ጀምሮ የተካሄዱ ምርምሮች የተበታተኑ በመሆናቸው ምን ያህል ጥልቀትና ሽፋን እንዳላቸው እምብዛም አይታወቅም፡፡ ገብረየሱስ ተክሉ እንዳመለከተው፣

> … እስካሁን የተካሄዱ የምርምር ሥራዎች የተበታተኑ፣ በርስ በርስ ማጣቀሻ ረገድ ድክመት ያላቸው፣ ለተመራማሪዎች እና አንባቢዎች ተደራሽ ያልሆኑ ሆነው ተገኝተዋል፤ ሌሎች ደግሞ በምርመራ ረገድ ጥልቀት የሌላቸው እና በይዘትና እና በጂኦግራፊያዊ ሽፋን ረገድ ውሱንነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡
>
> "…existing research works are found to be scattered, poorly cross-referenced and out-of-the-reach of researchers and readers; while others are shallow in their investigative depth and limited in thematic and geographical coverage."[3]

በተጨማሪም፡

> አብዛኛዎቹ ጥናቶች የተበታተኑ፣ ተደራሽ ያልሆኑ፣ እና በበቂ ሁኔታ ማጣቀሻ የሌላቸው በመሆኑ፣ በትንታኔ ጥልቀት፣ በይዘት ትኩረት፣ በባህላዊ ዳራ እና በጂኦግራፊያዊ ሥፍራ ረገድ ስለ ሽፋናቸው አድማስ ያለው ዕውቀት አነስተኛ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ልማዳዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በበቂ ያልተዳሰሱ፣ በቂ ሽፋን ያላገኙ እና ብዙም (ወይም ምንም) ያልተጠኑ በመሆኑ በዚህ ረገድ በቂ የሆነ እውቀት የለም፡፡
>
> "Since most studies are scattered, inaccessible, and inadequately cross-referenced, little is known about their coverage in terms of analytical depth, thematic focus, cultural backgrounds, and geographic locations. In other words, comprehsnive knowledge is lacking about customary dispute resolution mechanisms that have been sufficiently explored, inadequately covered, and little/never studied."[4]

ይህም የምርምሮቹን ግኝቶችና ምክረ-ሀሳቦች ለፖሊሲና ሕግ ግብዓትነት መጠቀም አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ የዚህ ጥናት ወሰን እኤአ ከ1960ዎቹ እስከ 2021 ድረስ የታተሙ ምርምሮችን በሦስት በመክፈል፣ ማለትም እኤአ ከ1960ዎቹ እስከ 1970 አጋማሽ፤ ከ1970ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ እና ከ1990ዎቹ መጀመሪያ እስከ 2021 ድረስ የታተሙ በሚል ቀርቧል፡፡ በሕግ ባለሙያዎች የተሠሩ ምርምሮች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡

ነገር ግን በሥነ-ሰብእ (በአንትሮፖሎጂ)፤ ታሪክ፤ ሶሻል ወርክ እና ፖለቲካ ሳይንስ ዘርፍ የታተሙ ሥራዎች እንዲሁም በጉዳዩ ያልታተሙ ምርምሮች አልተፈተሹም፡፡

---

[3] Gebreyesus Teklu, 2014, "Popular Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia: Trends, Opportunities, Challenges and Prospects", *AJCR*, 14 (1) pp. 99-100.

[4] Gebre Yntiso *et al (eds)*, 2011, *Customary Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia.* Addis Ababa: The Ethiopian Arbitration and Conciliation Centre, p. 473.

ይህ ጽሑፍ በክፍል ሁለት እኤአ ከ1960ዎቹ እስከ 1970 አጋማሽ፤ በክፍል ሦስት እኤአ ከ1970ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ፣ በአራተኛው ክፍል ደግሞ እኤአ ከ1990ዎቹ መጀመሪያ እስከ 2021 የታተሙ ምርምሮች፣ በመጨረሻም መደምደሚያና ምክረ-ሓሳብ በሚል ተዋቅሯል።

ያልታተሙትን ማግኘት ለዚህ ጸሐፊ አዳጋች ስለሆነ ለሕትመት በበቁት ላይ ትኩረት ተደርጓል። ከታተሙትም መካከል የዚህ ጽሑፍ አድማስ በሕግ ተመራማሪዎች ሥራ ላይ እንዲወሰን የተደረገው በሌሎች ሙያዎች ምሁራን የተሠሩት ጥናቶች ከዚህ ጸሐፊ ሙያዊ ትኩረት ውጭ በመሆናቸው ነው። በዋናነት በሕግ ባለሙያዎች ለተሠሩ ምርምሮች ሽፋን የተሰጠ ቢሆንም፣ የሕግና ሥነ-ሰብእ ባለሙያዎች በጥምረት የሠሯቸው ሥራዎች ታይተዋል። እኤአ ከ1960ዎቹ እስከ 2021 በታተሙት ምርምሮች ላይ ፍተሻ ለማድረግ በዚህ ጽሁፍ የተመረጡት መሥፈርቶች፣ ምርምሮቹ የተከተሉት ጥናት ዘዴ፤ ሽፋንና ጥልቀት፤ የምርምሩ በጀት ድጋፍ ሰጭዎች፣ እንዲሁም በምርምሮቹ የተነሱት ዋና ዋና ጭብጦች ናቸው።

## 2. እኤአ ከ1960ዎቹ እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ

በታወቁ ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ጆርናሎች ከ1960ዎቹ እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ ለሕትመት የበቁ ከሀያ በላይ የምርምር ጽሁፎች በዚህ ክፍል በጥቅሉ ተፈትሸዋል። የእነዚህ ጽሁፎች የተለየ ቀለምና ልዩ ትኩረት ከግምት ውስጥ ሳይገባ በጥናት ዘዴ፤ ሽፋንና ጥልቀት፤ ባለቤትነትና በተነሱት ዋና ዋና ጭብጦች ላይ በማተኮር ጠቅለል ያለ ፍተሻ ተደርጓል።

### 2.1 የጥናት ዘዴ

ምርምሮቹ በዋነኛነት እኤአ በ1960ዎቹ የወጡት ሕብረ-ሕግጋት ልማዳዊ ሕግጋትን ማካተት አለማካተታቸውን በመፈተሽ ላይ ያተኮሩ ነበሩ። የልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማትን ባህሪና ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ አካባቢ ተኮር የመስክ ጥናት እምብዛም አይታይባቸውም። የዚህም ዋናው ምክንያት ምርምሮቹ የተሠሩት በጊዜው ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርስቲ (የአሁኑ አዲስ አባባ ዩኒቨርስቲ) ሕግ ፋክልቲ ስለነበርና ፋክልቲው የተሰጠው ተልእኮ ሕብረ-ሕግጋቱን ማስተማርና ምርምር መሥራት ከመሆኑ ጋር ይያያዛል።[5] በሌላ አነጋገር የወቅቱ የመንግሥት ሥርዓት የልማትና ሕግ እሳቤ የመንግሥት ሕግን ውጤታማ ማድረግ የሚለውን መሠረት ያደረገ ነበር። የዚህም መነሻ የኢትዮጵያ የፖለቲካ አንድነት ማስጠበቂያ እንዲሁም የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እድገቷ የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ የሚያገለግለው የሕግ አንድነቷ ነው የሚል ይመስላል። በሁለተኛ ደረጃ በምክንያትነት የሚጠቀሱት የገንዘብ እጥረት፤ የተማራማሪዎቹ የቋንቋ ተግዳሮት እና ለሀገሩና ለባህሉ እንግዳ መሆን ናቸው። ነገር ግን መስክ ቀመስ ምርምር በወቅቱ በፍጹም አለተከናወነም ማለት አይደለም።[6]

---

[5] Stanley Fisher, 2014, "50 Years of Legal Education in Ethiopia: A Memoir" *Journal of Ethiopian Law*, vol. 26; Kaius Tuori, 2010, "Legal Pluralism and Modernization: American Law Professors in Ethiopia and the Downfall of the Restatements of African Customary Law", *Journal of Legal Pluralism, no 62*

[6] Norman Singer (1970-1971), "A Traditional Legal Institution in a Modern Legal Setting: The Atbia Dagnia of Ethiopia" *UCLA L. Rev.* vol. 18; Stanley Fisher, 1966, "Some

### 2.2 ሽፋንና ጥልቀት

ጥናቶቹ ጥቅልና ጭብጥ ተኮር ስለነበሩ የእያንዳንዱን ማኅበረሰብ ልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማትን ወደ ማጥናት አላተኮሩም። እንዲሁም የልማዳዊ ሕግ ሥርዓትን መሠረታዊና ሥነ-ሥርዓት ሕግጋትን እንዲ (substantive and procedural laws) ተቋማዊ ገጽታዎቻቸውን (institutional aspect) አልተመለከቱም። በዚህም የተነሳ ከማኅበረሰብ ባህላዊ የሕግ ሥርዓትና ጭብጥ አኳያ ሲታዩ ጥናቶቹ ክፍተት ይታይባቸዋል።

### 2.3 የምርምሩ በጀት ድጋፍ

እስከ እኤአ 1970ዎች አጋማሽ የተጠኑ ጥናቶች በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ሕግ ፋክልቲ ያስተምሩ የነበሩ የውጭ ሀገር የሕግ ምሁራን በፎርድ ፋውንዴሽን በተደረገላቸው የገንዘብ ድጋፍ የተከናወኑ ናቸው።[7] ከፎርድ ፋውንዴሽን በተጨማሪ ከስኮትላንድና ከቤልጂየም መንግሥታት የምርምር ገንዘብ ተገኝቶ ነበር።[8] በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም አገር በቀል ድርጅት ድጋፍ ተሠርቶ ለሕትመት የበቃ በጉዳዩ ላይ የተከናወነ ምርምር መኖሩን የሚያመለክት መረጃ ይህ ጸሐፊ አላገኘም። ይህም ተመራማሪዎቹ፣ ምርምሩና ገንዘቡ ከውጭ ምንጭ የተገኙ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

### 2.4 የተነሱ ዐበይት ጭብጦች

ጥናቶቹ በዋነኛነት ያነሷቸው ጥያቄዎች በሀገሪቱ እኤአ ከ1957 እስከ 1965 የወጡት ሕብረ ብሔር ሕግጋት ምን ያህል ልማዳዊ ሕግጋትን አካተዋል? ይህ በቂ ነው ወይ? ልማዳዊ ሕግጋት በምን ምን ጉዳዮች ላይ የሰፋ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል? በምን ምን ጉዳይ ቦታ ሊሰጣችው አይገባም? ለምን? ልማዳዊ ሕግጋት በዘመናዊ ሕግጋት በበቂ መልኩ ያልተካተቱበት ምክንያት ምንድነው? እነዚህ ዘመናዊ ሕግጋት በማሕበረሰቦች ውስጥ ምን ያህል ዘልቀው ገብተዋል ወይም ዘልቀው እንዲገቡ ምን መደረግ አለበት? ወዘተ የሚሉ ነበር።[9]

ምርምሮቹ በአብዛኛው የዘመናዊነት እሳቤ (የሞደርናይዜሽን ቲዎሪ) ውላጅ በሆነው ሕግና ልማት በሚባለው አስተሳሰብ ተጽዕኖ ሥር የወደቁ ነበሩ። የሕግና ልማት እሳቤ ልማት ለማምጣት የመንግሥት ሕግ አማራጭ የሌለው መሣሪያ ነው፣ ልማዳዊ ሕግጋት ግን ለሀገር ልማትና አንድነት መሰናክል ናቸው የሚል እምነት ያራምድ ነበር።[10] በመሆኑም ምርምሮቹ የሕግ ትምህርትን፣ ምርምርንና ሥልጠናን በመጠቀም ሕብረ-

---

Aspects of Ethiopian Arrest Law: The Eclectic Approach to Codification", *Journal of Ethiopian Law*, 3 (2)

[7] Jayanth Krishnan, 2012, "Academic SAILERS: The F Academic SAILERS: The Ford Foundation and the Efforts to Shape Legal Education in Africa, 1957-1977", *American Journal of Legal History*, Vol. 52

[8] Ibid; Kaius Tuori, 2010, cited above.

[9] George Krzczunowicz, 1966, "The Law of Filiation under the Civil Code", *Journal of Ethiopian Law*, 3 (2); Jacques Vanderlinden, 1966, ''An Introduction to the Sources of Ethiopian Law from the 13th to the 20th Century'', *Eth. J. L.* 3 (1); Rene David, 1967, ''Sources of the Ethiopian Civil Code'', *Eth. J. L. 4 (2)*

[10] Yong-Shik Lee, 2017, "General Theory of Law and Development", *Cornell International Law Journal*, 50 (3), https://scholarship.law.cornell.edu/cilj/vol50/iss3/2

ሕግጋትን መውጤታማ ማድረግ (ማለትም የሀገር አንድነትንና ልማትን ማምጣት) የሚቻልበትን መንገድ መዘየድ ቀዳሚ ዓላማቸው ነበር ማለት ይቻላል። ያም ሆኖ ግን፣ በአንዳንድ ውሱን ጉዳዮች የመንግሥት ሕግ ሥርዓት ያለበትን የሕግ ክፍተትና የተደራሽነት እጥረት ለመቅረፍ ልማዳዊ ሕግጋት ጥቅም ሊሰጡ እንደሚችሉ እሳቤው ያምናል።

በአንፃሩም፣ ሕብረ-ሕግጋቱን የህልም ሕግጋት ናቸው ምክንያቱም አንዳንድ ድንጋጌዎች አንዳንዴ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው፤ ሕጎቹ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ወደ ጎን ገሸሽ አድርገዋል የሚሉ ተቾቶችን የተወሰኑ ምርምሮች አቅርበዋል። ከዚህ በመነሳት ልማዳዊ ሕግጋት የበለጠ እንዲካተቱ መክረዋል። ልማዳዊ ሕግጋት ራሳቸውን ችለው ዋና የሀገሪቱ የሕግ ሥርዓት አካል ይሁኑ የሚል ምክረ-ሓሳብ ግን አልሰነዘሩም። የመጠን ጉዳይ ነው እንጂ እነዚህ የኂለኞቹ ጽሁፎችም ከዘመናዊነት ንድፈ ሓሳብ (Modernization Theory) እና ከልማትና ሕግ (Law and Development) እሳቤዎች ተጽዕኖ ያልተላቀቁ ነበሩ።

ምርምሮቹ እንደሚያሳዩት ሌሎች አፍሪካውያን በወቅቱ በዘመናዊ ሕግና በልማዳዊ ሕግ ምርጫ ተወጥረው በነበሩበት ወቅት ኢትዮጵያ ግን ሳታወላውል ሕግጋትዋን የማዘመን አማራጭን የተከተለችበት ጊዜ ነበር። ይህን በተመለከተ የሚከተለውን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፦

> ከነፃነት በኂላ የአፍሪካ ሀገራት በአንድ በኩል ባህላዊ ቅርስ የሆነውን የአፍሪካ ልማዳዊ ሕግ ሥርዓት ለመጠበቅ በነበራቸው ስሜት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዘመናዊነት፣ ዕድገት እና በአገር ግንባታ ፍላጎቶች መካከል በሚሰነዘሩ ተቃራኒ ግፊቶች መካከል ለመወሰን ይጥሩ በነበረበት ወቅት፣ በአንፃሩ በኢትዮጵያ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የምዕራባውያን ሕግ መርሆዎችን መሠረት ያደረገ የፍትሐ ብሔር ሕግ መውጣቱ እና ተግባራዊ መሆኑ ከአዲስ አበባ እና ከሌሎች ጥቂት ከተሞች ወሰን ውጭ ሕግን በእጅጉ የሚሽር ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል።
>
> While “after independence African countries were often torn between the contradictory impulses of preserving the traditional African legal heritage and the demands of modernization, progress, and nation building”, in Ethiopia, “[t]he last few years have shown that the enactment and attempted application of a Civil Code based on principles of western law… has led to severe nullification of the law outside the bounds of Addis Ababa and a few other cities”…[11]

የሀገሪቱ ፍትሐ ብሔር ሕግ አርቃቂ ፕሮፌሰር ሬኔ ዳቪድ የሚከተለውን ብለዋል።

> ኢትዮጵያ በጥብቅ የተቆራኘችባቸውን አንዳንድ ባህላዊ እሴቶቿን በመጠበቅ፣ የሕዝቧን የአኗኗር ዘይቤ እንኳ ጨምሮ መዋቅሮቿን ሙሉ በሙሉ ማሻሻል ትፈልጋለች። ስለሆነም ኢትዮጵያውያን አዲሱ ሕግ ... በተግባር ላይ የሚገኙ የልማዳዊ ሕግጋት ስብስብ ይሆናል ብለው አይጠብቁም። [የፍትሐ ብሔር ሕጉ] የሕብረተሰቡን ሁለንተናዊ ለውጥ የሚያመላክት መርሀ ግብር እንዲሆን ይሻሉ፤

[11] Schiller, 1966, as quoted in Kaius Tuori cited above p. 45 & 48.

እናም በአብዛኛው ወደፊት ሊፈጥሩ ለሚሹት ሕብረተሰብ ተስማሚ የሆኑ አዳዲስ ሕጎችን [የፍትሐ ብሔር ሕጉ] እንዲደነግግ ይፈልጋሉ፡፡

"While safeguarding certain traditional values to which she remains profoundly attached, Ethiopia wishes to modify her structures completely, even to the way of life of her people. Consequently Ethiopians do not expect the new Code to be a work of consolidation … of actual customary rules. They wish it to be a program envisaging a total transformation of society and they demand that for the most part, it set out new rules appropriate for the society they wish to create."[12]

ንጉሡም በዚህ ረገድ እንደሚከተለው የገለፁት መጤው ሕግ የአንድነት ኃይልና ወጥነትን የማስፈን ዓላማ እንዳለው የሚያመለክትና ይህን ነጥብ የሚያጠናክር ነው፡-

ሕግ በአንድ ሀገር ውስጥ የአንድነት ኃይል ነው፡፡ ዘመናዊ ሕብረ-ሕጎችንና ሌሎች ሕጎችን የማውጣት ግቦች ከሆኑት መካከል አንዱ ሕጉ በመላው ግዛት (ኢምፓየር) አንድ ወጥ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡

"Law is a unifying force in a nation: one of the goals sought to be attained by the enactment of modern codes and other legislation is that the law be uniform throughout the Empire."[13]

የሚከተሉት የፍትሐ ብሔር ሕግ እና የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዐት ሕግ ድንጋጌዎችም ከላይ የተጠቀሱትን የፍትሐ ብሔር ሕግ ዋና አርቃቂና የንጉሡን ሐሳቦች የሚያጠናክሩ መሆናቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

"ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በዚህ በፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች፣ ከዚህ በፊት በልማድ… ይሠራባቸው የነበሩ ደንቦች ሁሉ በዚህ የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለተተኩ ተሽረዋል፡፡"[14]

"ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በዚህ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች፣ በልምድ… ይሠራባቸው የነበሩ ደንቦች ሁሉ በዚህ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ስለተካተቱ በሙሉ ተሽረዋል፡፡"[15]

ሕብረ-ሕጋጋቱ ከፀደቁ ከአሥር ዓመት በኋላ ምን ያህል ሕዝቡ እየተጠቀመባቸው ነበር የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እኤአ በ1970ዎቹ የተደረጉ ጥናቶች የሚያሳዩትን እውነታ መመልከት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ካውስ ታዎሪ፣ "ማናቸውም ሕግ የሰዎችን መብትና ግዴታ ለመግለጽ እንዲሁም በመካከላቸው ያሉት ግንኙነቶች የሚተዳደሩበትን መሠረታዊያን ሐሳቦች ለመግለጽ የወጣ ሲሆን፣ ሕጉ ከወጣላቸው ሰዎች ልብ የሚደርስ ፍላጎታቸውን፤ ልማዳቸውን ወይም የተፈጥሮ ፍትሕን የሚጠብቅ ካልሆነ በቀር ዋጋ

[12] Rene David, 1963, "A Civil Code for Ethiopia: Considerations on the Codification of the Civil Law in African Countries", *Tul. L. Rev.* 37 (2) p. 193.

[13] *Haile Sellassie I,* 1964, p. v England, Bath.

[14] የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 165/1952፣ አንቀጽ 3347 (1)

[15] የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዐት ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 52/1958 መግቢያ

ሊኖረው አይችልም፣"[16] "... no legal tradition will live in writing if it is not part of the social reality" በማለት አስገንዝበዋል።[17]

በወቅቱ የተከናወኑ ምርምሮችን ውጤታማነት በተመለከተ ሁለት ዐበይት ክርክሮች ይቀርባሉ። አንዳንዶች ምርምሮቹ (የሕግ ትምህርትን ጨምሮ) በሀገሪቱ የግለሰቦች መብት እንዲከበርና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን የመሠረት ድንጋይ የተጣለበት አድርገው ይወስዱታል። "[Legal research and education of the time] helped to lay a foundation fo continued growth and development of Ethiopia`s legal system, and for the rule of law."[18] ሌሎች ደግሞ የሀገሪቱን ባህላዊ ሕግጋት በማጥፋት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን ለማስፋፋት የተደረገ በጎ ሓሳብ የነበረው ነገር ግን የተጨናገፈ እብሪተኛና ገራገር ፕሮጀክት አድርገው ያቀርቡታል።[19]

## 3. እኤአ ከ1970ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ

በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ ልማዳዊ ሕግጋት ላይ በሕግ ተመራማሪዎች የታተመ ሥራ አናገኝም። ለዚህም በምክንያትነት ሊቀርቡ የሚችሉት፣ ከኢትዮጵያ አብዮት ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሕግ ፋክልቲ በጉዳዩ ምርምር ያደርጉ የነበሩ የውጭ ሀገር መምህራን ወደ ሀገራቸው መመለስ፤ ለምርምር ይውል የነበረው የውጭ የገንዘብ እርዳታ ከዚሁ ጋር አብሮ መቋረጥ እና በጊዜው ከነበረው የመንግሥት ርዕዮተ-ዓለም ጋር በተገናኘ ለሕግና ለሕግ ምርምር የተሰጠው አነስተኛ ቦታ ናቸው። ሕግና ልማት የሚለው አስተሳሰብ በተለያዩ ምክንያቶች እየተዳከመ መጥቶ ነበር። የውጭ ገንዘብ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የማስፋፊያ መሣሪያ ነው በሚል በጥርጣሬ ይታይ ነበር። በፊውዳሉ ሥርዓት ከውጭ የተቀዱትን ሕግጋት ርዕዮተ-ዓለማዊ መሠረቶች አብዮቱ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ስለከተታቸው በእነሱ ላይ ምርምር መሥራት ያልፈለገም ይመስላል። በዚህ ወቅት ከሕግ ሙያ ውጭ ባሉ ተመራማሪዎች የታተሙ ምርምሮች ቢኖሩም እጅግ ውስን ናቸው።

## 4. እኤአ ከ1990ዎቹ እስከ 2021

### 4.1 የጥናት ዘዴ

በእነዚህ ዓመታት የተከናወኑ ምርምሮች ሕጉን ብቻ ከመፈተሽ (doctrinal research) ባለፈ ማህበረሰብ ተኮር የመስክ ጥናቶች አካተው ይታያሉ። የመስክ ምርምሮቹ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶችን ከምንጫቸው ድረስ በመሄድ ቀልፍ መረጃ ሰጪዎችን በማነጋገርና ምልከታ በማድረግ የማጥናት ዝንባሌ ይታይባቸዋል።

### 4.2 ሽፋንና ጥልቀት

በጥናቶቹ ከሀምሳ በላይ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሽፋን አግኝተዋል። አንዳንዶቹ ምርምሮች የዳሰሳ ጥናቶች ስለሆኑ ጥልቀት ያንሳቸዋል። ሌሎቹ ደግሞ ጭብጥ ተኮር በመሆናቸው ክፍተት ይታይባቸዋል። አንዳንዶቹ ምርምሮች በአንድ ብሔረሰብ ላይ

[16] Civil Code of Ethiopia of 1960 Preface, Para 2
[17] Kaius Tuori, 2010, cited above p. 62.
[18] Stanley Fisher, 2014, cited above p. 204.
[19] Jayanth Krishnan, 2012, cited above

በተደጋጋሚ የተሠሩ ናቸው። ይህም ያልተጠኑ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ልማዳዊ ሕግጋት መኖራቸውን ያመለክታል።

> ከዚህ ቀደም በባህላዊ ግጭት አፈታት ዘዴ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እና በዚህ ቅጽ ላይ የተካተቱ ጥናቶች የሚሸፍኑት የኢትዮጵያን ሕዝብ የተወሰነ ክፍል ብቻ መሆኑን ተገንዝበናል። በባህላዊ ግጭት አፈታት ዘዴዎች ሥር ከሚሸፈኑ ጉዳዮችም መካከል በጥናቶቹ የተሸፈኑት ጥቂት ናቸው። ይህም የሚጠቁመው በጥናቶቹ ባልተካተቱት የባህላዊ ግጭት አፈታት ዘዴዎች እንዲሁም ጥናቱ ያልሸፈናቸውን ማህበረሰቦች በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የላቀ ሰፋት ያለው ሥራ እንደሚያስፈልግ ነው።
>
> "Our observation is that previous studies on CDRM (Customary Dispute Resolution Mechanism) and the studies in this volume cover only a portion of the Ethiopian population. They also cover only a few of the items that fall within the mandate of CDRMs. This hints the need for a more comprehensive work on the CDRMs of the uncovered areas as well as uncovered items in the different communities."[20]

### 4.3 የምርምር በጀት ድጋፍ

እነዚህ ምርምሮች በማን የገንዘብ እርዳታ ነው ተሠርተው ለሕትመት የበቁት? የሚል ጥያቄ ሲነሳ፣ በሲዳ፣ በፈረንሳይ ኤምባሲ፣ በዩኤንዲፒ፣ በፒስካፕና በኖርዌ ኤምባሲ የሚል መልስ እናገኛለን። በተወሰነ መልኩም በመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች የገንዘብ ድጎማ በድህረ-ምረቃ ተማሪዎችም የተሠሩ ጥናቶች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል። የምርምሮቹን የገንዘብ ምንጭ ለማወቅ የሕትመቶቹን የምስጋና ገጽና የመጀመሪያ ገጽ የግርጌ ማስታወሻ መመልከት በቂ ይሆናል።

### 4.4 የተነሱት ዋና ዋና ጭብጦች

የምርምር ጽሁፎቹ የሚከተሉትን አሥር ዐበይት ጭብጦች አስተናግደዋል።[21]

#### 4.4.1 በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ሲባል ምን ማለት ነው?

ለዚህ ጥያቄ በምርምር ጽሁፎቹ ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል። በአገራችን ሁኔታ የሕግ ሥርዓት ሲባል እኤአ በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ የታወጁትን ስድስት ሕብረ ሕግጋት (law codes)፣ እንዲሁም የእነርሱ ውላጅ የሆኑትን ዘመናዊ የሕግ ተቋማትና መዋቅሮች ከነማሻሻያቸው ይጨምራል። እነዚህን ሕግጋትና ተቋማት ተከትለው ባለፉው ግማሽ ምዕተ ዓመት የታወጁት አገር አቀፍና የክልሎች ሕግጋት፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና እነዚህን ተከትለው የተፈጠሩት የሕግ ተቋማት በዚሁ ምድብ የሚካተቱ ናቸው።

[20] Gebre Yntiso *et al* (eds), 2011, cited above

[21] በዚህ ንዑስ ክፍል የተብራሩት ዐበይት ጭብጦች የተወሰዱት በሚከተለው መጽሐፍ ውስጥ በጸሐፊው በተዘጋጀው የመግቢያው ንዑስ ክፍል (ለ) ከተገለጹት በከፊል ነው። (*የባሕል ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጵያ* ቅጽ 1፣ የፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት፣ አዲስ አበባ፣ ኤልያስ ኑር እና ሙራዱ አብዶ (አርታኢዎች)፣2007 ዓ.ም/እኤአ 2015

ነገር ግን ይህ የኢትዮጵያን የሕግ ሥርዓት ሙሉ ሥዕል እንደማይሰጠን ይታወቃል። በሕብረ-ሕግጋቱ እና ከዚያም ቀጥለው በታወጁ ሕግጋት እውቅና የተሰጣቸው ኃይማኖታዊና ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማትም የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት አካላት ናቸው። የአገሪቱ የሕግ ሥርዓት አድማስ ከዚህም ያለፈ ነው። ምክንያቱም በዘመናዊው የመንግሥት ሕግጋት ይሁንታ ያላገኙና ያልተካተቱ አያሌ ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማት እንዳሉ ይታወቃል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት እነዚህንም ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማት ይመለከታል። ከዚህ የሕግ ብዝሀነት አንፃር የኢትዮጵያ የሕግ ምህዳር በነጠላ *የሕግ ሥርዓት* ተብሎ ከሚገለጽ ይልቅ *የሕግ ሥርዓቶች* ቢባል ይመረጣል።

ይህም ሕግ ምንድነው? ወደሚለው ትልቅ ጥያቄ ያመራናል። በኢትዮጵያ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ ገጠር የሚኖር እንደመሆኑ፣ እንዲሁም በየዓመቱ ከሚከሰቱ 7.4 ሚሊዮን የሕግ ጉዳዮች (ችግሮች) ውስጥ 83 በመቶ የሚሆኑት ክርክሮች በአማራጭ የፍትሕ መስጫ መንገዶች በተለይም በባሕላዊ የሕግ ሥርዓት መፍትሔ የሚያገኙ ከመሆናቸው አኳያ፣ ማለትም፣ 17 በመቶ የሚሆነው ጉዳይ ብቻ መደበኛ ተብሎ ወደ የሚጠራው የፍትሕ ሥርዓት የሚያመራ[22] መሆኑ፣ ሰፊ የሆነ የሕግ ጽንሰ-ሓሳብ እንድንይዝ ያስገድደናል።

በዚህ ረገድ ፕሮፌሰር ኖርማን ሲንገር፣ ሕግን በመተርጎም ረገድ ሰፊ አድማስ ወዳለው የሕግ እሳቤ በመሸጋገር ኅብረተሰብ አግባብነት ባለው፣ ውጤታማ በሆነና መስተጋብር በተሞላበት አኳኋን እንዲራመድ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።[23] ይህ እጅግ ሰፊ የሕግ እሳቤ ሲሆን፣ ያንኑ ያህል ደግሞ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ መሆናቸውን መገንዘብ ያሻል።[24]

### 4.4.2 ልማዳዊ የሕግ ሥርዓትና ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎች

በምርምር ጽሁፎቹ የተነሳው *ሁለተኛ* ነጥብ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓት ከሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎች ጋር ሊጣጣም የሚገባ መሆኑ ነው። በሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች መሠረት (ሀ) ከኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ማናኛውም ሕግ ወይም ልማድ ተፈጻሚነት አይኖረውም፤ (ለ) ሴቶች ከጎጂ ባህል ተጽዕኖ የመላቀቅ መብት አላቸው፤ (ሐ) ይህንኑ የሴቶች መብት መንግሥት የማስከበር ኃላፊነት አለበት፤ (መ) ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሯቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፤ እንዲሁም (ሠ) ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ መንግሥት የመርዳት ኃላፊነት ያለበት መሠረታዊ መብቶችን፤ ሰብዓዊ ክብርንና ዴሞክራሲን እስካልፃረሩ ድረስ ነው የሚሉት ነጥቦች ተሰምሮባቸዋል።

መወገድ የሚገባቸውን የልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማት ገጽታዎች፣ ለምሳሌ የሴቶችን ሰብአዊ መብቶች የሚጋፉ ተግባራት (ዕድሜ ሳይደርስ ጋብቻ፤ የሴት ልጅ ግርዛት፤

---

[22] HiiL, 2020, "Justice Needs and Satisfaction in Ethiopia: Legal Problems in Daily Life" https://www.hiil.org/wp-content/uploads/2019/09/JNS_Ethiopa_2020-1.pdf Accessed April 22, 2022

[23] Norman Singer, July 2008, "Three Eye-opening Events", *Mizan Law Review*, 2:2, p. 344.
"we [ought to] grow toward having a wider conception of legal rules as set of norms and processes that enable a society to function properly, effectively, and harmoniously"

[24] የኢፌዴሪ ሕግ መንግሥት፣ አንቀጽ 9 (1); አንቀጽ 35 (4) እና አንቀጽ 91(1) ይመለከቷል።

በጋብቻ ወቅትና ጋብቻ ሲፈርስ ሴቶች በንብረት ላይ ያላቸው መብት የተጣበበ መሆን፤ የጠለፋ ጋብቻ፣ እንዲሁም በፍርድ ሂደት ሴቶችንና ወጣቶችን አሳታፊ በማደረግ ረገድ ያሉትን ክፍቶተች፣ ወዘተ) ምርምሮቹ በሚገባ ለይተዋል፡፡ ምርምሮቹ እነዚህ ጉድለቶች የሚወገዱበትን ስልት በተመለከተ የጠለቀ ምርምር የማከናወን፤ ዘመናዊ ትምህርት የማስፋፋት፤ ሕግ የማሻሻልና የመተግበር፤ እንዲሁም ለነዚህ ተግባራት የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ተሳትፎ የሚመለከቱ ዋና ዋና ስልቶችንም አመልክተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ከልማዳዊ ድርጊቶች መካከል የተወሰኑትን ለይቶ ለማስወገድ መስፈርት እንደሚያሻ ግልጽ ተደርጓል፡፡ የሚወገዱትን ልማዳዊ ሕግጋት ለመለየት የሚያገለግሉን መስፈርቶች ግን በሚገባ ትንታኔ አልተሰጣቸውም፡፡ በምርምር ጽሑፎችና በተለያዩ ሀገራት ሕግጋት የምናገኛቸው መመዘኛ መስፈርቶች የልማዳዊ ሕግጋት ከሰብዓዊ መብት ያለመቃረን፤ ከፍትሕና ሞራል ጋር መጣጣም፤ ለሀገር አንድነት እንቅፋት ያለመሆን፤ ከዲሞክራሲ መርሆዎች ጋር መናበብ እንደ ሕጻናትና ሴቶች ባሉ ተጋላጭ የሕብረተሰቡ አካላት ላይ ጉዳት ያለማድረስ የሚሉ ሁነው እናገኛቸዋለን፡፡ የትንታኔው አስፈላጊነትም የሚመነጨው ከእነዚህ መስፈርቶች አሻሚና አወዛጋቢ መሆን ነው፡፡

ጎጂ ልማዶችንና የሚወገዱበትን ዘዴ ከመለየት ባሻገር በማህበረሰቡ እግር ተተክቶ እነዚህን መወገድ ያለባቸው ልማዶች ማህበረሰቡ ለምን እንደፈጠራቸው የማወቁ ጉዳይ በእነዚህ ጥናቶች ሽፋን አላገኘም፤ ነገር ግን ይህ ጉዳይ እነዚህን ልማዶች እንዳናስወግዳቸው ምክንያት ይሆነናል ለማለት ሳይሆን ቢቻል ከሕብረተሰቡ ምንም ተቃውሞ የማያስነሳ ወይም አነስተኛ ተቃውሞ ብቻ የሚያስነሳ የማስወገጃ ዘዴ ለመዘየድ ፋይዳ አለው ለማለት ነው፡፡ ለአንድ ችግር ፍቱን መድኃኒት ማግኘት ይቻል ዘንድ በሚመለከተው ማህበረሰብ እግር ተተክቶ ጉዳዩን መመርመር አስፈላጊ ስለመሆኑ፣ አንድ ታዋቂ የወባ በሽታ ሊቅ ትንኞችን የመቆጣጠር ፍላጎት ካለን እንደ ትንኞች ማሰብን እንደምንማር በተምሳሌት ያስተምሩናል፡፡[25]

### 4.4.3 የልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማት ትርጉም

ስለልማዳዊ ሕጎች በተደረጉ ጥናቶች የምናገኘው ሦስተኛ ጭብጥ ስለልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማት ፍቺ የተሰጠ መሆኑን ነው፡፡ ከአንድ ማኅበረሰብ ልማድ የመነጩ አስገዳጅነት ያላቸው ድንጋጌዎች ባህላዊ ሕግጋት በመባል ይታወቃሉ፡፡ አስገዳጅነት እንዳላቸው በማሰብ ለረጅም ጊዜ የማኅበረሰቡ አባላት ተቀብለው የተገበሯቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ወረድ ብለን እንደምንገልጸው ልማዳዊ ሕግጋት ሳይለወጡ ይዘልቃሉ ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ ሕግጋት በአብዛኛው ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ሲተላለፉ የመጡ ናቸው፡፡ ባህላዊ ሕግጋት ከቦታ ቦታ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ባህላዊ ሕግጋትን አለመከተል ቅጣትን ወይም ካሳ መክፈልን ያስከትላል፡፡ ነገር ግን በእስር፤ በገንዘብ ወይም በሞት መቀጣትን ዋና ዓላማቸው አያደርጉም፡፡ የሻከረውን ወንድማማችነትና እህትማማችነት ወይም ጉርብትና እንዲታደስ በማድረግ እርቅና ሰላም

---

[25] "If you wish to control mosquitoes, you will learn to think like mosquitoes".
Samuel Darling as quoted in Benjamin Paul, 1955, *Health, Culture and Community: Case Studies of Public Reactions to Health Programs* (New York: Russel Sage Foundations), p. 1.

ማውረድ ዐብይ ዓላማቸው ነው። በመሆኑም የልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማት መሠረት የሆኑት ይቅር ባይነት፤ ባህልን ማክበር፤ እውነትን መናገር፤ በሰላም አብሮ መኖር እና ሰብአዊ ክብርን መጠበቅ፣ እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ እሴቶች በጽሁፎቹ ተለይተው እናገናቸዋለን።

እርቅ አላወርድም ያለ ወገን ከቅጣቶች ሁሉ የከፋ ሊሆን የሚችለው ማኅበራዊ መገለል እንደሚጠብቀው ተጠቁሟል። ለአብነት አቶ ሰላሙ በቀለ የመገለልን ቅጣት ከባድነት ከሞት ቅጣት ጋር ከማመሳሰል በተጨማሪ፤ ከሰው ተራ አውጥቶ ከዱር አራዊት ጋር የሚቀላቅል ተግባር በሚል እንዲህ ይገልጹታል፦

> የግለሰብ ጥፋት ማኅበራዊ ኑሮን የሚያናጋ ሲሆን መጀመሪያ ከተግባሩ እንዲቆጠብ ይመከራል፤ አልተው ሲል ከማኅበሩ እንዲለይ ይደረጋል። ይህም የሞት ቅጣት (ነው)። ይህ ቅጣት የደረሰበት [ግለሰብ] ሌላ ማኅበረሰብ ፈልጎ አግኝቶ እዛ መኖር ስለማይችል ኑሮው ብቸኛ ሰው ሆኖ ከዱር አራዊት ጋር ይሆናል ማለት ነው።[26]

እነዚህ ባህላዊ ሕግጋት ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ መዋቅሮች ባህላዊ የፍትሕ ተቋማት በሚል ይታወቃሉ። በማኅበረሰቡ ዘመናዊ መንግሥት ያልተመሠረተ ከሆነ ወይም ዘመናዊ መንግሥት ተመሥርቶም የመንግሥት ሕግ የማስፈጸም አቅሙ ደካማ ሲሆን የባህላዊ ተቋማት ሚና የላቀ ነው። የመንግሥት የፍትሕ ሥርዓት ጠንካራ በሆነበትም ሁኔታ እነዚህ ተቋማት በተጓዳኝ ህልውና ሲኖራቸው ይስተዋላል። በሕግጋቱ ብቻ ሳይሆን በተቋማቱም ላይ ጥናቶቹ ትኩረት በማድረግ፤ አደረጃጀታቸውን፣ የባሕላዊ ዳኝነትን እርከን፤ የዳኝነትን ማዕቀፍ፤ የዳኞችን ማንነት፤ እንዲሁም የሥልጣናቸውን ምንጭና የሥራ ዘመን የሚፈትሹ ናቸው። የፍርድ ሂደትንም በተመለከተ ቅድመ-እርቅ፤ የእርቅ ሂደት (ጉዳይ ማጣራት፤ የችሎት አካሄድ፤ ውሳኔ አሰጣጥና ቅጣት) እና ድህረ-እርቅ (የማሳረጊያ ደንብና የውሳኔ አፈጻጸም) ሥርዓቶችን ይመረምራሉ። በተጨማሪም በሀገራችን በሚገኙት በርካታ ልማዳዊ ሕግጋትና ሥርዓቶች መካከል ያለው ልዩነት ብቻ ሳይሆን አንኳር የጽንሰ-ሓሳብ እና የእሴት አንድነትንም የሚያመላክቱ ናቸው።

### 4.4.4 የባህላዊ ሕግጋትና ሥርዓቶች ፖሊሲ ስለመቅረጽና ሕግ ስለ ማውጣት

የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ባህላዊ ሕግጋትና ሥርዓቶችን በተመለከተ እውቅና የቸሩ ድንጋጌዎችን ቢያካትትም፤ ድንጋጌዎቹን ሥራ ላይ ለማዋል በፌደራልም ይሁን በክልል ደረጃ እስካሁን ድረስ ፖሊሲ አለመቀረጹና ሕግ አለመውጣቱ ከጥናቶቹ የሚታይ አራተኛ ጭብጥ ነው። በዚህም የተነሳ ለምሳሌ ያህል በባህላዊና በመደበኛ ፍርድ ቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገዛ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ የለም። የባህል ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ፤ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የሚጣጣሙ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ መንግሥት የመርዳት ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም፣ መንግሥት ልማዳዊ ተቋማት እንዲያድጉና እንዲጠበቁ እኩል ድጋፍ ያደርጋል የሚለው ኃላፊነት ምን ማለት እንደሆነ በዝርዝር የሚገልፅና ይህን ወደ ተግባር የሚያሸጋግር ሕግ አልታወጀም። ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ሚና የሚደነግግ፣ እንዲሁም በልማዳዊና በመንግሥት የፍትሕ ተቋማት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት የሚገልፅ የሕግ ማዕቀፍም የለም። በሌላ አገላለጽ አግባብነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ከመመርመር አንፃር፤ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ለልማዳዊ የሕግ

[26] ሰላሙ በቀለ፣ 2001፣ *ሕግን እንወቅ* (አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ)፣ ገጽ፣ 35

ሥርዓቶች የተሰጠው እውቅና ክፍተት እንደሚታይበት፤ ለምሳሌ ልማዳዊ ተቋማት ከመደበኛ ፍርድ ቤቶችና ከመንግሥት አስተዳደር አካላት ጋር ሊኖራችው የሚገባው ግንኙነትና የሥልጣን ወሰናቸው ግልጽ አይደለም የሚሉትን ነጥቦች የምርምር ጥናቶቹ በሚገባ አመልክተዋል።

ነገር ግን ጥናቶቹ ያልተመለከቷቸው ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህም ጉዳዮች መካከል በሕገ መንግሥቱ ለልማዳዊ ሕጎች የተሰጠውን እውቅና በቂነት በሚመለከት ለምሳሌ ልማዳዊ የወንጀል የፍትሕ ሥርዓቶች ቦታ አላቸው ወይ? ዝርዝር የሕግ ማዕቀፉ መውጣት ያለበት በፌዴራል ሕግ አውጪ አካል ነው ወይንስ በክልል? ሕገ መንግሥቱን ተከትለው የወጡ ፖሊሲዎችና አዋጆች ለልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማት ምን ያህል ቦታ ሰጥተዋል? የሚሉት ጥያቄዎች ይገኙባቸዋል። ከቀበሌና ወረዳ አስተዳደሮች ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል? ከወረዳና ዞን ፍርድ ቤቶች፤ ፖሊስና ዐቃቤ ሕግ ጋርስ? ባህላዊ ሽማግሌዎች በሕዝቡ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነትና ተአማኒነት የሚያሳጣ ግንኙነት ከአካባቢያቸው አስተዳደር ጋር የማድረግ ዝንባሌዎች ይታያሉን? ጉዳይ ተኮር የተዳቀለ ሕግ ወይም ተቋም (ለምሳሌ የባህላዊና ዘመናዊ ፍርድ ሂደት የሚስተዋልባቸው በአሁኑ ሰዓት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሥራ ላይ የምናገኛቸው የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ኮሚቴዎች) የሚፈጠርበት ሁኔታ ይስተዋላልን? ይህ ለሁለቱ ሥርዓቶች ግንኙነት ምን አንድምታ ይኖረዋል? የሚሉና የመሳሰሉት ጥያቄዎችም ሊጠኑ ይገባል።

ልማዳዊ ሕግጋትን የሚገዛ ሕግ አልወጣም፣ ፖሊሲም አልተቀረጸም ማለት ምንም ጥረት አልተደረገም ማለት አይደለም። ለማለት የተፈለገው አንድ ወጥ ፖሊሲና ሕግ አልወጣም ነው። ከሕግጋት መካከል ለምሳሌ ባህላዊ ሕግጋትና ሽማግሌዎችን መጠቀም የሚያስችሉትን የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጆችን መጥቀስ ይቻላል። ከፖሊሲ ደግሞ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ[27] እና የባሕል ፖሊሲን ማየት ይቻላል። በተጨማሪም አንዳንድ ልማዳዊ ሕግጋት ላይ ብይን የሰጡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎችን መመልከት ይቻላል። እነዚህ ሕግጋት፤ ፖሊሲዎችና የሰበር ችሎች ውሳኔዎች በጥናቶቹ አልተነሱም።

በጥናቶቹ የተስተናገደው ሌላው ተያያዥ ጉዳይ የመንግሥት ሕግና ባህላዊ ሕግጋት ይፋዊ ያልሆነ መስተጋብር ያላቸው መሆኑ ነው። የዚህ ምንጭም ሁለቱ የሕግ ሥርዓቶች በጊዜ፤ በቦታና በጉዳይ ጎን ለጎን ሲኖሩ (ወይም co-exist ሲያደርጉ) ስለሚታይ ነው። በዚህ የተነሳ አንዱ በሌላው ላይ ተፅዕኖ ሲፈጥር፤ አንዱ የሌላውን ጽንሰ-ሐሳብና ዘዴ ሲወርስ ይስተዋላል። በአንድ በኩል ባህላዊ ሕጎችንና ተቋማትን በዚያው ማኅበረሰብ እይታ መመርመር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከመንግሥት ሕግ ጋር ያላቸውን መስተጋብር መገንዘብ በዘርፉ የሚደረጉ ጥናቶችን ዘዴ በመምረጥ ረገድ አንድምታ አላቸው። ስለሆነም ሰነዶችን፤ ሕግጋትንና ቀደምት ጥናቶችን ከመጠቀም በተጨማሪ፤ መረጃ መሻት ያለብን ለማጥናት በመረጥነው አካባቢ ከሚገኙ እንስትና ተባዕት ሽማግሌዎች፤ ወጣቶች፤ ተመራማሪዎች እንዲሁም ደግሞ በመንግሥት ፍትሕ ሥርዓት ከሚገኙ ሰዎች ጭምር ነው። በሌላ አገላለጽ ልብ ሊባል የሚገባው፣ ልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማት ከመደበኛው የሕግ ሥርዓት ጋር ስላላቸው ተግባራዊ መስተጋብር (interface) በሚገባ የአለመጠናቱ ጉዳይ ነው።

[27] ፍትሕ ሚኒስቴር፣ "የኢፌዴሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ" የካቲት 25፣ 2003 ዓ.ም.

በተግባር የሁለቱ መስተጋብር አንዳንዴ ውድድር (ፉክክር) አንዳንዴ ደግሞ ትብብር ይታይበታል።[28] በአንዳንድ ቦታዎች የሚታይና ይፋዊ በሆነ ፖሊሲ ያልተደገፈ የሁለቱ ሥርዓቶች መስተጋብር የልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶችን ቅቡልነት በሚሸረሽር መልክ እየተደረገ ስለሚመስል ይህ ተገቢ እንዳልሆነ ምርምሮቹ ይመክራሉ። የሁለቱ ሕግ ሥርዓቶች የሚተባበሩበት ዘዴ በምርምሮቹ ውስጥ እንብዛም አልተጠቆመም። ንጽጽራዊ ጥናት በማድረግ ለምሳሌ ብዙ ርቀት የተጓዙ የሌሎች አፍሪካ አገራት ተሞክሮዎችን ምርምሮቹ ሲያነሱ አይስተዋልም።

### 4.4.5 የባህላዊ ሕግጋትና ሥርዓቶች ሕገመንግሥታዊ እውቂያ ተግባራዊነት

የጥናቶች *አምስተኛውና* ሌላው ዐብይ ሓሳብ ለባህላዊ ሕግጋትና ተቋማት እውቅና መስጠት፤ በእነሱ ላይ ጥናት ማድረግ፤ እንዲያድጉና እንዲበለጽጉ መንግሥታዊ ድጋፍ ማድረግ የማስፈለጉን ምክንያት መመርመር ነው። ይህን ጉዳይ መሣሪያዊ ጠቀሜታ (instrumental function) እና የማንነት ጉዳይ ብለን በሁለት ልንመድበው እንችላለን። የመጀመሪያው ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማትን በመሣሪያነታቸው ወይም ከሚሰጡት ተጨባጭ ጥቅም አንፃር ሲመለከታቸው፤ የኋለኛው አተያይ ግን እንደ መሣሪያ ሆነው ባገለገሉን መጠን የምናነሳቸው፤ የማይጠቅሙን ሲመስለን አውልቀን የምንጥላቸው ሳይሆኑ፤ የማኅበረሰብ የጋራ ክብር በመሆናቸው ብቻ (the fact that they form a community`s collective dignity) ቦታ ይሰጣቿል። እነዚህ ሁለት አስተሳሰቦች በአጭሩ እንደሚከተለው ተብራርተዋል።

#### ሀ) *ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማትን እንደ መሣሪያ የመመልከት አስተሳሰብ*

ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማት የአንዲት አገር የሕግ ማሻሻያ መሠረት ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይገባልም። ይህ ተግባር እውን ሊሆን የሚችለው አገሪቱ በባህልዋ የመጠቀም ፍላጎትና ቁርጠኝነት ሲኖራት እንዲሁም ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማት የሕግ ማሻሻያ በሚደረግበት ወቅት ወይም ቀደም ብሎ በጹሑፍ ሰፍረው የተገኙ ከሆነ ነው። ለአብነት ያህል ፈረንሳይ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ማክተሚያና በ19ኛው ክፈለ ዘመን መባቻ አምስት ሕብረ-ሕግጋትን (law codes) በቀረጸችበት ወቅት የተጻፉ ባህላዊ ሕግጋት ስለነበሯት በሚገባ ልትጠቀምባቸው ችላለች። ነገር ግን ከፈረንሳይ አንድ መቶ ሀምሳ ዓመት ዘግይታ ስድስት የተጻፉ ሕብረ-ሕግጋትን ያፀደቀችው ኢትዮጵያ ይህንን ዕድል አላገኘችም። ልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማትን በመንግሥት የሕግ ማዕቀፍ ማካተት የመንግሥትን የሕግ ሥርዓት ተቀባይነትና ውጤታማነት እንደሚጨምር በአንዳንድ ምሁራን በሰፊው የታመነበት ቢሆንም፤ እነዚህ ሕግጋት በበቂ ሁኔታ ቦታ አልተሰጣቸውም ነበር። ይህም ሊሆን የቻለው ልማዳዊ ሕግጋት እምብዛም በጽሑፍ ባለመስፈራቸው፤ የወቅቱ የሀገሪቱ ልሂቃን የዘመናዊነት አስተሳሰብ አራማጆች ስለነበሩና (ይህም አስተሳሰብ ልማዳዊ ሕግጋት ለአንድ ታዳጊ አገር አንድነትና ልማት አይበጁም የሚል ስለነበረ)፣ በተለይ ፕሮፌሰር ሬኔ ዳቪድና ሌሎች የሕግ አርቃቂዎች በጽንሰ-ሓሳብ ደረጃም ቢሆን ልማድ እንጂ ባሕላዊ ሕግጋት የሚባል ነገር እንደሌለ ያምኑ ስለነበር ነው። የኢትዮጵያን የፍትሐ ብሔር ሕግ አርቃቂ አቋም በተመለከተ ፕሮፌሰር ኖርማን ሲንገር እንዲህ ይላሉ፡-

> በፍትሐ ብሔር ሕግ እውቂያ ያገኘው ኦፊሴላዊ ሕግ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቸኛው ሕግ እንደሆነ ነው [ሬኔ ዴቪድ] የተሰማው። እንዲያውም ሕጋዊ እውቅና ከተሰጠው የሕብረ-ሕግጋት ሥርዓት ውጭ የነበሩት ሥርዓቶች እንደ ልማድ

[28] Gebre Yntiso *et al (eds)*, 2011, cited above

ብቻ የሚታዩ እንደነበሩ በተደጋጋሚ ገልጧል፡፡ ... በኢትዮጵያ ትይዩ ለሆነ የሕግ ሥርዓት እውቂያ አልነበረም፡፡… [ነገር ግን] አሁንም እንደማምነው፣ በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛዎቹ ባህላዊ የአለመግባባት መፍቻ ሥርዓቶች የሕግ ኃይል ሊሰጣቸው የሚያስችሉ ክፍለነገሮች አሏቸው፡፡

"[René David] felt that the official law recognized in the Civil Code was the only law in Ethiopia. In fact, he repeated a number of times that the systems that existed outside of the officially recognized Code system were just custom… In the case of Ethiopia … there was no recognition of the parallel system …, I still believe that most of the systems of traditional dispute settlement in Ethiopia possess the elements which give them the force of law."[29]

ልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማት በመንግሥት ሕግ ሳይካተቱ ራሳቸውን ችለው ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ሌላው አካሄድ ነው፡፡ ይህም በተራው የመንግሥት የፍትሕ አካላትን ያግዛል፤ ጫናቸውን ይቀንሳል፤ የፍትሕ ተደራሽነትን ያሰፋል፡፡ ልማዳዊ ሕግጋት በሕዝቡ ዘንድ ተመራጭ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ድብቅ የሆኑና በመደበኛው የሕግ ሥርዓት ሊታወቁ የማይችሉ ወንጀሎችን የመመርመሪያ ፍቱን ዘዴ አላቸው፤ እንዲሁም ልማትን በማምጣት በኩል ባህላዊ ሕጎችና ተቋማት አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ለልማት አስተዋጽዖ የሚያደርገው የመንግሥት ሕግ ብቻ እንደሆነ የመመልከት እሳቤ ሲቀየር ብቻ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ሕግና ልማት (law and development) ከሚለው እሳቤ ጋር የተቆራኘ ሲሆን፤ ሕግና የሕግ ተቋማት ማለት ከመንግሥት የሚመነጩት ብቻ ናቸው፤ ስለዚህ ልማት ለማምጣትና ልማትን ለማራመድ ዋናው ጉዳይ የመንግሥት ሕግጋትና ተቋማትን የበለጠ ተደራሽ፣ ምሉዕ እና ውጤታማ በማድረግ ማጠናከር ነው ከሚል እይታ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተብራራው እኤአ በ1960ዎቹ ገናና የነበረው የሕግና ልማት እይታ ባህላዊ ሕግጋትና ተማቋት ልማትን ማምጣትና ዘላቂ እንዲሆን ለማድረግ ሊረዱ ይቀርና እንቅፋቶች እንደሆኑ የሚቆጥር አስተሳሰብ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በሊጋል ፖዚቲቪዝም አስተምህሮት ውስጥ ለሕግ የበላይነት የተሰጠው ትርጓሜ ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማት የሚጫወቱትን ሚና ከግምት ያስገባ አይደለም፡፡ በፖዚቲቪዝም አስተሳሰብ የመንግሥት ተቋማትና ባለሥልጣናት ሕግን እንዲያከብሩ፤ ከሕግ በታች ሆነው ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ መደረግ ያለበት የመንግሥትን የሕግ ሥርዓት ብቻ በመጠቀም እንደሆነ ይገመታል፡፡ እነዚህ የሕግና ልማት እንዲሁም ፖዚቲቪዝም አስተሳሰቦች የባህላዊ የሕግ ሥርዓትን አስተዋጽዖ ከግምት ውስጥ አያስገቡም፤ የግለሰቦችን፣ የባህላዊ አመራሮች እና የተቋማትን ስምረትና ይህም ሕግን የተከተለ እና ተገማች የዜጎች ሕይወትን በተመለከተ ባህላዊ ሕግ የሚኖረውን ሚና አይገነዘቡም፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት እውነታዎች የባህላዊ ሕግጋትና ተቋማትን እንደ መሣሪያ ከመመልከት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ይህ መሣሪያዊ አመለካከት በአብዛኛዎቹ በዚህ ጽሁፍ በተዳሰሱ ምርምሮች ገኖ ይታያል፡፡ እንዲሁም ጥናቶቹ በቂ ፍተሻ ሳያደርጉ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ተደራሽና አሳታፊ ናቸው፤ ፍትሐዊና ወጪ

[29] Norman Singer, January 2008, cited above, pp. 144-145.

ቆጣቢ ናቸው፤ እንዲሁም የሰፋ ተቀባይነት አላቸው፤ ከሙስና የፀዱ ናቸው የሚሉ ድምዳሜዎች ላይ ሲደርሱ ይስተዋላል። እኤአ ከ1990ዎቹ በኋላ ከታተሙት ምርምሮች የተወሰኑት በልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶችና በሕግ የበላይነት መካካል መጣጣም መኖሩንና ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ለልማት የሚያበረክቱት አዎንታዊ አስተዋጽኦ መኖር ብቻ ሳይሆን እነሱን ሳይጠቀሙ ልማት ማምጣት አዳጋች እንደሆነ ይጠቁማሉ። ልማዳዊ ሕግጋትን ተጠቅመን የሕግ የበላይነትና ልማት እንዴት ማምጣት እንችላለን የሚለው ጭብጥም ላይ ተጨማሪ ፍተሻ ሊደረግበት ይገባል።

### ለ) *ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማት ከመሣሪያነት የዘለለ ጠቀሜታ ያላቸው ስለመሆኑ*

ከላይ እንደተመለከተው ባህላዊ ሕግጋትና ተቋማት ከማንነት ጋር ተያያዥነት አላቸው። በአንድ አገር ውስጥ የሚኖር ማኅበረሰብን ባህል ለመጠበቅ፤ ለማሳደግ፤ ለመንከባከብና ለማሻሻል ይረዳሉ። ይህ ፋይዳ የሚመነጨው ባህል የማኅበረሰብ ማንነት አሻራ አካልና መገለጫ በመሆኑ ነው። በዚህ ረገድ በስዋሂሊ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ዘንድ ጥልቅ የሆነ ትርጉም ያዘለውንና ኡቡንቱ (ubuntu) በመባል የሚታወቀውን ጽንሰ ሐሳብ ማስተዋል ይቻላል። የጽንሰ ሐሳቡ ትርጉም፤ "I am, because you are, because we are" ማለት ሲሆን፣ ይህም በግርድፉ "እኔ እኔን የሆንኩት፣ በአንተ/አንቺ፤ በእኛ ምክንያት ነው" በሚል ሊገለፅ ይችላል። ይህም የልማዳዊ ሕግጋትና ተቋማትን ጠቀሜታ ከማሳየት ባሻገር፤ የትውልድና የሰው ልጆችን ጥልቅ ቁርኝት፤ እንዲሁም ትናንት ከዛሬና ከነገ ጋር ያላቸውን ትስስር ይነግረናል። ከያዝነው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ይህ የኡቡንቱ መልዕክት የባህላዊ የሕግ ሥርዓትን በቅጡ እንድናውቀው፤ እንድንወርሰው እና እንድናወርሰው ዓይነተኛ ሚና ይኖረዋል። ሰፋ አድርገን ስናስተውለው ይህ ጎዳና አንድ ማኅበረሰብ "ማንነቴ ይከበር፤ እራሴን በራሴ ላስተዳድር፤ በራሴ ሕግና ተቋማት የመጠቀም መብትን ልጎናጸፍ" የሚሉ ጥያቄዎች እንዲያነሳ በር ይከፍትለታል።

የባህላዊ ሕግን አስፈላጊነት ከመሣሪያነቱ ወይም ከማንነት መገለጫነቱ አኳያ በመመልከት መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተጨማሪ ነጥቦች ሊነሱ ይችላሉ። ባህላዊ የሕግ ሥርዓትን እንደ መሣሪያ መቁጠር ይህንን ሥርዓት እንደ አንድ ሕዝብ መለያ ምልክት መውሰድን ላያመለክት ይችላል። በአንፃሩ ግን የተገላቢጦሹ ትክክል ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት ለምሳሌ ባህላዊ የሕግ ሥርዓት ማንነቱን ከማክበር ጋር በተገናኘ አንድ ሕዝብ እውቅና ሲሰጠው ባህላዊ ሥርዓቱ በመሣሪያነት የሚሰጠውን ጥቅም ሕዝቡ ይቋደሳል ማለት ነው። በሌላ በኩል ግን ባህላዊ የሕግ ተቋማት እንደ መሣሪያ ብቻ ከታዩ ከእነሱ የሚገኘው ጥቅም ሲቀንስ ወይም ቀሪ ሲሆን (ለምሳሌ ዘመናዊውን የሕግ ሥርዓት የበለጠ ተደራሽና ውጤታማ በማድረግ) ቸል ሊባሉ ወይም ጭራሹኑ ሊተዉ ይችላሉ። በዚህም የተነሳ ሁለተኛው ምክንያት በመርህ ላይ የተመሠረተና የበለጠ መሠረታዊ ይመስላል። በአንፃሩ የመጀመሪያው በፕራግማቲዝም እሳቤ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ለባህላዊ የሕግ ሥርዓት ቦታ ሊሰጥ የሚችለው "እንደ ሁኔታው" ነው።

### 4.4.6 ባህላዊ የሕግ ሥርዓት ራሱን ችሎ በጥልቀት እንዲጠና ስለማድረግ

በምርምሮቹ የታየው *ስድስተኛ* ገዥ ሐሳብ በዘርፉ ወደ ፊት የሚጠብቁንን ሰፊና ጠለቅ ያሉ ምርምሮች በምናካሂድበት ወቅት ሁለት ጉዳዮች ከግምት መውሰድ እንደሚገባን መገንዘብ ነው። አንደኛ ባህላዊ የሕግ ሥርዓትን ከመንግሥት የሕግ ሥርዓት ጋር ሳንቀላቅል ለብቻው በጥልቀት ማጥናት ይገባናል። ከመንግሥት የሕግ ሥርዓት ጋር የሚደረገው ንጽጽር በኋላ ቢመጣ ይመረጣል። ምክንያቶቱም ሁለቱ የሕግ ዓለማት ለምሳሌ በእይታ ልዩነት የተነሳ በዋና ዋና ጎዳዮች ላይ በአንድ የጋራ ልኬት የማይነፃፀሩ

(incommensurable) ሊሆኑ ይችላሉ። የአጥኚው ትኩረት ወደ ንጽጽር ሊሳብ ስለሚችል በባህላዊ ሕጉ ላይ የሚደረገው ምርምር ሊሳሳ ይችላል። የተጠናው ባህላዊ ሕግ ሕልውና የሚያገኘው ከዘመናዊው ሕግ ጋር በተመሳሰለ መጠን ነው የሚል እንደምታ ሊፈጥርም ይችላል።

በዚህ ፀሐፊ እምነት በተቻለ መጠን የጥናቱ መሠረት በሆነው ማኅበረሰብ ቦታ ሆነን (putting ourselves in their shoes) የባህላዊ ሕጎችንና ተቋማትን ማየት አስፈላጊ ነው። እዚህ ላይ ነጥቡ ይህ ሕግና የሕግ ሥርዓት በምን ምክንያት ተፈጠረ የሚለውን መፈተሽ ነው። ጥናቱ በእነሱ አተያይ መሠረት ከተከናወነ የሕጋቸውንና ሥርዓታቸውን መንፈስ በቅጡ እንረዳለን፤ ሌላውም እንዲረዳው መንገድ እንከፍታለን ማለት ነው። ሥርዓቱን በተገቢው መንገድ መረዳት ዓለም አሁን ከደረሰችበት ደረጃ ጋር የማይሄደውንና መቅረት ያለበትን በመረዳት ደካማ ገጽታዎችን ማስወገድ ያስችላል። ከባህል ሕጎችና ተቋማት መካካል ሊቀጥሉና ሊጠበቁ የሚችሉ ገፅታችዎችንም በተመሳሳይ መገንዘብ ይቻላል። ይህ ማለት ግን ባህላዊ የሕግ ሥርዓትን ያለበቂ ምክንያት ማወደስ አለብን ማለት አይደለም። ጀምስ ስኮት እንዳስገነዘቡት፡-

> [አካባቢያዊ፣ ባህላዊ እና ልማዳዊ ለሆኑ እውነታዎች ምክንያታዊ የሆነ አድናቆት አግባብነት አለው፤ ምክንያቱም] "አንዳንድ ሊበራሎች ለማጣጣል እንደሚሞክሩት ሳይሆን ከተግባራዊ እውቀት አንዳንድ ሥርወ ነገሮች ውጭ የመደበኛው የሥርዓት ፈለጎች ሊፀኑ አይችሉም። [ነገር ግን] ለአካባቢያዊ፣ ባህላዊ እና ልማዳዊ [ሥርዓቶች የሚደረግ ሂስ-አልባ አድናቆት] ሊጸና የማይችል ነው፤ ምክንያቱም ይህ አካሄድ ከዘመናዊው የሊበራል አስተሳሰብ ጋር ከማይጣጣሙ የጫና፣ የጠቅላይነትና የማግለል ተግባራት በአብዛኛው የማይለይ ነው።
>
> [A reasonable admiration of the local, the traditional, and the customary is sensible because] "formal schemes of order are untenable without some elements of the practical knowledge that the liberals tend to dismiss." [But uncritical admiration of] "the local, the traditional, and the customary" is untenable because it "is often inseparable from the practices of domination, monopoly, and exclusion that offend the modern liberal sensibility.[30]

በዚህ ረገድ ቢጋናና በአካባቢዋ የሚኖሩት የአካን ሕዝቦች ትምህርት ይሰጡናል፤ ባህላችውን ሳንከፋ በምትባል ወደኋላ እያየች ወደ ፊት በምትራመድ ምናባዊ ወፍ ይመስሉታል። ከመልዕክቱ የምንገነዘበው ባህላችን ወደፊት ከመሄድ ወይም ለውጥ ከመቀባል ማለትም አንዳንድ የባህላችንን ገጽታዎች ከመተው ሊገታን እንደማይገባ፤ እንዲሁም የመጣንበትን መርሳት እንደሌለብን ነው። በአንፃሩ፣ በዚህ ጽሁፍ በተቃኙት አንዳንድ ምርምሮች ልማዳዊ ሕግጋትን በዘመናዊው ሕግ መነጽር የማየት ዝንባሌ ተስተውሏል።

[30] James Scott, 1998, *Seeing Like A State: How Certain Schemes to Improve the Human Condition Have Failed*, (New Haven and London, Yale University Press), p. 7.

### 4.4.7 የባህላዊ ሕግ ሥርዓት አድማስ ከግጭት አፈታት የሰፋ ስለመሆኑ

በምርምር ጽሑፎች ይዘት ረገድ ሊነሳ የሚገባው *ሰባተኛ* ነጥብ ጽሁፎቹ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶችን እንደግጭት መፍቻ መሣሪያ ብቻ አድርጎ የማቅረብ ሰፊ ዝንባሌ የሚታይባቸው መሆኑ ነው። ይህም ማለት ግጭት በመከላከል ረገድ ባላቸው ፋይዳ ላይ ተገቢውን ትኩርት አልሰጡም። ሕልው ሕግጋት

### 4.4.8 የባህላዊ ሕግ ሥርዓት እየተለወጠ የሚሄድ ስለመሆኑ

ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች እየተለወጡ መሆናቸውና እንደነበሩ ሊቀጥሉ እንደማይችሉ ምርምሮቹ የሚያስረዱ መሆኑ ከጽሑፎቹ የምንገነዘበው ስምንተኛ ነጥብ ነው። ማለትም ልማዳዊ ሕግ ማህበራዊ ተግባራዊነት ያለው ሕግ ("living law") መሆኑን ያስገነዝባሉ። ይህም ጥያቄ ባህል ምንድነው ወደሚለው ነጥብ ይወስደናል። ባህል የማይለውጥ ባለበት የሚረግጥ አለመሆኑን እንረዳለን። ለምሳሌ በትግራይ ክልል ሴቶች በማህበራዊ ፍርድ ቤቶች እንዲሳተፉ መደረጉ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ገጠሮች ሴትን የደፈረ በሽማግሌዎች ለመንግሥት አሳልፎ የመስጠት ልማድ ባህል በበጎ መልኩ ሊለወጥ እንደሚችል ያሳየናል። ይህ ለውጥ በጎ ያልሆነ ገጽታም ሊያመጣ ይችላል፤ ለምሳሌ አቅምን ያላገናዘበ የአገልግሎት ክፍያ መጠየቅ፤ ለጎሳ አባል ማዳላት፣ ወዘተ ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች ተአማኒነትን ሊሸረሽሩ የሚችሉ ናቸው። ጽሁፎቹ ከዚህ አኳያ ባህል ምን እንደሆነ አልተነተኑም፤ በዚህ ረገድ የደቡብ አፍሪካ ተመራማሪዎች ያደረጉት ጥረት ተጠቃሽ በመሆኑ ልንማርበት ይገባል።

### 4.4.9 በግለሰብና ቤተሰብ ጉዳዮች ተግባራዊ እየሆነ ያለው የሸሪአ ሕግ ሥርዓት

በፌዴራል ሕገ መንግሥቱ ለሸሪአ ፍትሕ ሥርዓት እውቅና ከመሰጠቱ አንፃር በሀገራችን የሕግና ፍርድ ቤቶች የአሠራር መስተጋብር ረገድ ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ተግዳሮቶች በምርምሮቹ እጥረት የሚታይ መሆኑ የምርምር ጽሑፎቹን የሚመለከት *ዘጠነኛ* ነጥብ ነው። በአገራችን በተለያዩ ቦታዎች በግለሰብና ቤተሰብ ጉዳዮች ተግባራዊ እየሆነ ያለው የሸሪአ ሕግ ሥርዓት ከልማዳዊ ሕግ ሙሉ በሙሉ የተላቀቀና ኃይማኖታዊ ይዘት የተላበሰ ነው የሚል በከፊል የተሳሳተ ግምት የዚህ ጉድለት መንስኤ ይመስላል። ነገር ግን በተግባር ሁለቱ የቅልቅል ይዘት አላቸው።

በመሆኑም ስለልማዳዊ የሕግ ሥርዓት ስንመራመር ኃይማኖታዊ የሕግ ሥርዓቶችን ወደ ጎን ገሸሽ ማድረግ ተገቢ አይመስልም። በሀገሪቱ ውጤታማ የሆነ የጋራ የሕግ ሥርዓት ለማረጋገጥ፣ አንደኛ ከሸሪአ ፍርድ ቤት ዳኞች አቅም በተለይም የሸሪአ ሕግና ዘመናዊ ሕግ ከማወቅና ፍርድ ቤቶቹ ከመንግሥት ፍርድ ቤቶች ካላቸው ነፃነት አንፃር የሸሪአ ፍትሕ ሥርዓት ምን ያህል ባህሪውን ጠብቆ እየሄደ መሆኑን በየጊዜው ምን ያህል እየፈተሸን ነው የሚለው ጭብጥ ትኩረት ይሻል። ሁለተኛ የሸሪአ ፍትሕ ሥርዓት በተግባር ሕገ መንግሥታዊ ስታንዳርዶችን በመጠበቅ ረገድ እንዴት ይታያል የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው። ይህ መነሻ መስፈርት (minimum standard) መሟላቱ ሊረጋገጥ የሚችለው እነዚህ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸው ውሳኔዎች ከሕገ መንግሥቱ ጋር የተጣጣሙ መሆን አለመሆናቸውን በመፈተሽ ነው። የሕገ መንግሥትን ጉዳይ የሚመለከቱ ተቋማት ምን ያህል ይህንን ሥራ ለማከናወን የሚያስችል አቅም ገንብተዋል

የሚል ተያያዥ ጭብጥም ይነሳል።[31] እንዲሁም የሸሪአ ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ወሰናቸውን በተግባር እንዴት እየተረዱት ነው?[32] ከዚህም በተጨማሪ፣ ተከራካሪ ወገኖች በተለይም ሴት ተከራካሪዎች የሸሪአ ፍርድ ቤቶችን የመጠቀም አዝማሚያ ምን ይመስላል? እና በፍርድ ቤቶቹ የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት አተገባበር ምን ያህል ደረጃውን የጠበቀ ነው የሚሉ ጥያቄዎችን መፈተሸ ይገባል።[33]

### 4.4.10 ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ተፈላጊነታቸው የመጨመሩ ምክንያት

ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች እኤአ ከ1990ዎቹ ጀምሮ ተፈላጊነታቸው ለምን ጨመረ ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት አንፃር ጥናቶቹ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በተገቢው ሁኔታ ፈትሸው አልተገኙም። በአሁኑ ወቅት የማንነት ፖለቲካ መንገስ (የሕዝቦች የራስን እድል በራስ መወሰን መብት ማንሰራራት)፣ ይህን ተከትሎ የግጭቶች መባባስና እነዚህን ግጭቶች ለመፍታት ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶችን የመጠቀም አዝማሚያ መታየት፣ የታዳጊ አገሮችን የመንግሥት ሕግ ሥርዓቶች ለማጎልበት የዓለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች ለበርካታ አሥርተ አመታት በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ቢመድቡም ለልማት ያበረከተው አስተዋጽኦ ውስን ሆኖ መገኘቱ፣ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ለልማት ሊያግዙ ይችላሉ በማለት ፊታቸውን ወደ እነሱ ማዞራቸው፣ እኤአ በ1990ዎቹ የሰብአዊ መብት እንቅስቃሴ መንገሥን ተከትሎ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች የሰብአዊ መብት ጥሰት ምንጮች ተደርገው መቆጠራቸው ፍተሻ የተደረገባቸው የምርምር ነጥቦች ናቸው።[34] በዳሰሳው የተካተቱት ምርምሮች ሰብአዊ መብቶች ለልማዳዊ ሕግጋት ያላቸውን አንድምታ ቢመለከቱም፣ የማንነት ፖለቲካንና በቅርቡ የዓለም አቀፍ ልማት ድርጅቶች እየሰጡ ያሉትን ትኩረት በበቂ አልተመለከቱም።

## 5. መደምደሚያና ምክረ-ሐሳብ

ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ያልተጻፉ፣ ከቦታ ቦታ የሚለያዩ፣ ኋላ ቀር፣ ለሀገር ልማትና አንድነት እንቅፋት ስለሆኑ መወገድ ያለባቸው ናቸው የሚለው አስተሳሰብ እየተዳከመ ነው። የመብት ጥሰቶች የማያስከትሉ ልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶች ፍትሕን ተደራሽ በማድረግ፣ ልማት በማምጣትና የሕግ የበላይነትን በማስፈን በኩል ጠቃሚ መሆናቸውን የሚገልፀውና፣ መወገድ ያለባቸው የመብት ጥሰት የሚያደርሱት ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ብቻ ናቸው የሚለው አስተሳሰብ የላቀ ተቀባይነት እያገኘ ነው።

---

[31] Girmachew Alemu, 2015, "Legal and judicial plurality and the incorporation of traditional dispute resolution mechanisms within the state justice system" in *Non-state justice institutions and the law*, Springer pp. 20-22

[32] Federal Courts of Sharia Consolidation Proclamation 188/1999

[33] Mohammed Abdo, 2020, "Federal Sharia Courts in Addis Ababa their administration and the application of law in the light of recent developments" in Epple, S., & Getachew Assefa (eds) *Legal Pluralism in Ethiopia: Actors, Challenges and Solutions* (Culture and Social Practice). Bielefeld: transcript Verlag. https://doi.org/10.14361/9783839450215, p. 159.

[34] Caroline Sage and Michael Woolcock (eds), 2006, *The World Bank Legal Review Law, Equity, and Development*, vol. 2, The World Bank

በዚህ ጽሁፍ የተቃኙት ምርምሮች የአንድ ሕዝብ ባህላዊ የሕግ ሥርዓት ከዚያ ሕዝብ ባህል ይቀዳል፤ እሱን ማወቅ አገርንና ሕዝብን ለማወቅ በር ይከፍታል የሚል ሓሳብ ያራምዳሉ ሊባል ይችላል። ይህ ሓሳብ በሌላ አገላለጽ ምኒልክ በተሰኘው ታሪካዊ ተውኔቱ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን አፄ ምኒልክን ተመስሎ ለልጅ እያሱ ከሚለግሰው ከሚከተለው ምክር ጋር ይመሳሰላል፡-

> ሰው በተለይም የመንግሥት ኃላፊነት ያለው ሰው ባለው ነገር ላይ እንጂ፤ በተጨባጭ በሚዳሰሰውና በሚጨበጠው ነገር ላይ እንጂ፤ በሚመኘውና በሚያልመው የሓሳብ እስትንፋስ ላይ ዓላማውን ሊያዋቅርና ሊገነባው አይችልም። … ባህልህን አጠንክረህ ካላወቅህ አገርህም አያውቅህ! ሕዝብህንም አታውቅ! ሕዝብህን ማወቅ ማለት የሕዝብህን ባህል ብልት ጠንቅቀህ መገንዘብ ነው። ሕዝብህን ማወቅ ደግሞ አገርህን ማወቅ ነው። ማንነቱን ያላጤንክለትን ሕዝብ ነገ ማስተዳደሩ ያቅተሃል- እያሱ።…[35]

ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች እውቅና ሊሰጣቸው የሚገባው በመሣሪያነታቸው ነው ወይንስ የማህበረሰብ ማንነት መገለጫ በመሆናቸው የሚለው ጥያቄ አልተጤነም። በልማዳዊ ሕግ ሥርዓትና በመንግሥት ሕግ ሥርዓት መካከል ያለውን ተግባራዊ መስተጋብርም ጥናቶቹ በበቂ አልፈተሹም። ለሕግ ማሻሻያ ግብዓት እንዲሆኑ፤ አሁን ያለው ትውልድ እንዲጠቀምባቸው፤ ለመጪው ትውልድም ተጠብቀው እንዲተላለፉ በሚል መንግሥት እራሱ የመራው፣ ፋይናንስ ያደረገውና በጉዳዩ ላይ የተከናወነ የምርምር ሥራ አልታየም።

አንትሮፖሎጂስቶች፤ ሶሺያል ዎርከርስ፤ የታሪክና ፖለቲካ ሳይንስ ባለሙያዎች በልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶች ላይ ያካሄዷቸው ምርምሮች በዚህ ጽሁፍ ስላልታዩ ሊፈተሹ ይገባል። ያልተጠኑ ልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች፤ እንዲሁም ተጠንተውም በጥልቀት ያልተኬደባቸው ስላሉ በእነዚህም ላይ ምርምር ሊደረግ ይገባል። በተለያዩ የውጭ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ የሚሠሩ ጥናቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ መንግሥት እራሱ የሚመራውና በገንዘብ የሚደግፈው በልማዳዊ ተቋማት ላይ የሚደረግ ምርምር እንዲኖር ያስፈልጋል። ይንንም የሚያከናውን ተቋም ሊኖር ይገባል። በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፤ በአዋጆችና በፖሊሲዎች ለልማዳዊ ሕግጋት የተሰጠው እውቅና በቅጡ ሊፈተሽ ይገባል። ልማዳዊ ሕግ ሥርዓቶችን የሚመለከት ፖሊሲና ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ መቅረጽ እንደሚያስፈልግ ጥናቶቹ ያቀረቡት ምክረ-ሓሳብ ተገቢ ነው።

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ከመግቢያው ጀምሮ ለባህላዊና ኃይማኖታዊ የሕግ ሥርዓቶች እውቅና የሚሰጡ በርካታ ድንጋጌዎችን ማካተቱ ይታወቃል።[36] ስለዚህ ይህ ሕገ መንግሥት የሕግ ብዝሀነትን የተቀበለ ሰነድ ነው። ይህ እንደ ጥንካሬ የሚታይ ቢሆንም፣ ከዚህ የሕግ ብዝሀነት እሳቤ ጋር በተያያዘ ሊፈተሹ የሚገቡ ነጥቦች አሉ። አንደኛ ከሕገ መንግሥቱ መርሆዎች የማይቃረኑ ልማዳዊ ወይም ኃይማኖታዊ ድንጋጌዎች በተዋረድ በሚወጡ የፌዴራልም ይሁን የክልል ሕጎች ሊሻሩ ይገባል ወይ? ሁለተኛ ሕገ መንግሥቱ ለልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች የሰጠው የእውቅና ወሰን ውስንነት የለበትም ወይ? ሦስተኛ ሕገ መንግሥቱ ከልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ጋር በተቆራኘ የፌዴራልና የክልልን ሥልጣን በሚገባ ለይቶ አስቀምጧል ወይ? አራተኛ ከልማዳዊ የሕግ ሥርዓቶች ጋር በተገናኘ ሕገ መንግሥቱ እስከምን ድረስ ለአንድ የማህበረሰብ

---

[35] ጸጋዬ ገብረ መድኅን፣ 2003፣ *ታሪካዊ ተውኔቶች፣* (አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ) ገጽ 273

[36] የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መግቢያ፣ አንቀጽ 9፣ 34፣ 35፣ 39፣ 78 እና 91

አባል ባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ የሕግ ሥርዓቱን የመተው ወይም የመቀበል ነፃነት ሊሰጠው ይገባል? በመጨረሻም ሕገ መንግሥቱ ከፀደቀ ጀምሮ የፌዴራል መንግሥት አዎንታዊ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የሕግ ሥርዓቶችን በማጎልበት ረገድ ምን ያህል ሠርቷል? አሉታዊ የሆኑትስ ቀሪ እንዲሆኑ የተከናወኑ ሥራዎች ጥንካሬና ክፍተት ምን ይመስላል? የሚሉት ዐበይት ጭብጦች ምርምር ይሻሉ፡፡[37]

ትልቁን ሥዕል ለማየት ስንሞክር በዚህ ጽሁፍ ዳሰሳ የተደረገባቸው ምርምሮች በንጉሡ ጊዜ ኢትዮጵያ የፖለቲካ አንድነቷ ማስጠበቂያ እንዲሁም የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እድገቷ የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ የሚያገለግለው የሕግ አንድነቷ ነው የሚል እሳቤ እናገኛለን፡፡ የሕግ አንድነት ሲባል ከምዕራቡ ዓለም የተቀዱ ዘመናዊ ሕግጋትን ታሳቢ ያደረገ ነበር፡፡ ይህም በከፊል ካፒታሊዝም ከፊል ፊውዳሊዝም እሳቤ ላይ ተመሥርቶ፣ ሀገሪቱ ወደ ካፒታሊዝም ጎዳና እንድታመራ የፈለገ ይመስላል፡፡ በደርግ ዘመንም የፖለቲካና የሕግ አንድነት ለሀገር ልማት ወሳኝ መሆኑ ተቀባይነት አግኝቶ ቀጥሎ ነበር፡፡ የፖለቲካ አንድነት ግራ ዘመም፤ የሕግ አንድነቱ ደግሞ ሶሻሊስታዊ የሕግ ሥርዓት ላይ ያነጣጠረ ነበር፡፡ በዘመነ ኢሕአዴግ የነበረው ሕገ መንግሥትና ሕግን አሳምሮ በመግለጽ ደረጃ (constitutional and legal rhetoric)፣ ያልተማከለ የፖለቲካና የሕገ ሥርዓት በአጠቃላይ የሕግ ብዝሀነት በተለይ ለልማት መሠረት ነው በሚል እሳቤ ላይ የተንጠለጠለ ነበር፡፡ በዚህ ትርክት መሠረት የንጉሡና የደርግ ዘመነ መንግሥታት የዘመናዊነት ትርክት ተከታዮች ሲሆኑ፣ ዘመነ ኢሕአዴግ ደግሞ የድህረ ዘመናዊነት ቲዎሪ ገጽታዎች ማለትም የልዩነት፣ ብዝሀነት፣ የተካታችነትና አካታችነት (difference, heterogeneity, multiplicity, inclusion and exclusion) ባህሪያትን የተላበሰ ነበር ያሰኘዋል፡፡[38] ይህ ልዩነት ወደ ኃይል፣ ሁከትና ብጥብጥ ሳያመራ ማኅበረሰቦች በሠለጠነ መንገድ ሊጠቀሙበት ይችሉ ዘንድ አንድ-ዓለማዊ (cosmopolitan) አመለካከትን በማስረፅ ተቻችሎ መኖር እንዴት ይቻላል የሚለው እንደ ዐብይ ተግዳሮት ሊታይ የሚገባ ይመስላል፡፡ ■

[37] የኦሮሚያ ክልል የባህል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋምና እውቅና ለመስጠት የወጣ አዋጅ ቁጥር 240/2013 ይዘትና አፈጻጸሙን መገምገም ጠቃሚ ሲሆን ይችላል፡፡

[38] Ronald Bleiker, 2015, "Posmodernism" in Richard Devetak *et al (eds) An Introduction to International Relations*, Cambridge University Press

# የተጠቀሱ ጽሑፎች (Cited References)

## (በግርጌ ማስታወሻ የተጠቀሱ)

Bleiker, Ronald, 2015, "Posmodernism" in Richard Devetak *et al (eds) An Introduction to International Relations*, Cambridge University Press

David, Rene, 1963, ''A Civil Code for Ethiopia: Considerations on the Codification of the Civil Law in African Countries'', *Tul. L. Rev.* 37 (2).

Fisher, Stanley (2014), "50 Years of Legal Education in Ethiopia: A Memoir" *Journal of Ethiopian Law*, vol. 26; Kaius Tuori, 2010, "Legal Pluralism and Modernization: American Law Professors in Ethiopia and the Downfall of the Restatements of African Customary Law", *Journal of Legal Pluralism, no 62*

Gebre Yntiso *et al (eds)*, 2011, *Customary Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia.* Addis Ababa: The Ethiopian Arbitration and Conciliation Centre.

Gebreyesus Teklu, 2014*, '*Popular Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia: Trends, Opportunities, Challenges and Prospects", *AJCR*, 14 (1).

Girmachew Alemu, 2015, "Legal and judicial plurality and the incorporation of traditional dispute resolution mechanisms within the state justice system" in *Non-state justice institutions and the law*, Springer.

*Haile Sellassie I,* 1964, England, Bath.

HiiL, 2020, "Justice Needs and Satisfaction in Ethiopia: Legal Problems in Daily Life" https://www.hiil.org/wp-content/uploads/2019/09/JNS_Ethiopa_2020-1.pdf, accessed April 22, 2022

Krishnan, Jayanth, 2012, "Academic SAILERS: The F Academic SAILERS: The Ford Foundation and the Efforts to Shape Legal Education in Africa, 1957-1977", *American Journal of Legal History*, vol. 52

Krzczunowicz, George, 1966, "The Law of Filiation under the Civil Code", *Journal of Ethiopian Law*, 3 (2); Jacques Vanderlinden, 1966, ''An Introduction to the Sources of Ethiopian Law from the $13^{th}$ to the 20th Century'', *Eth. J. L.* 3 (1); Rene David, 1967, ''Sources of the Ethiopian Civil Code'', *Eth. J. L. 4 (2)*

Lee, Yong-Shik, 2017, "General Theory of Law and Development", *Cornell International Law Journal*, 50 (3),

https://scholarship.law.cornell.edu/cilj/vol50/iss3/2

Mohammed Abdo, 2020, "Federal Sharia Courts in Addis Ababa their administration and the application of law in the light of recent developments" in Epple, S., & Getachew Assefa (eds) *Legal Pluralism in Ethiopia: Actors, Challenges and Solutions* (Culture and Social Practice). Bielefeld: transcript Verlag. https://doi.org/10.14361/9783839450215, p. 159.

Paul, Benjamin, 1955, *Health, Culture and Community: Case Studies of Public Reactions to Health Programs* (New York: Russel Sage Foundations), quoting Samuel Darling

Sage, C & Woolcock, M (eds), 2006, *The World Bank Legal Review Law, Equity, and Development*, vol. 2, The World Bank

Scott, James (1998), *Seeing Like A State: How Certain Schemes to Improve the Human Condition Have Failed*, (New Haven and London, Yale University Press).

Singer, Norman, 1970-1971, "A Traditional Legal Institution in a Modern Legal Setting: The Atbia Dagnia of Ethiopia" *UCLA L. Rev.* vol. 18; Stanley Fisher, 1966, "Some Aspects of Ethiopian Arrest Law: The Eclectic Approach to Codification", *Journal of Ethiopian Law*, 3 (2)

Singer, Norman, 2008, "Three Eye-opening Events", *Mizan Law Review*, 2:2.

**ሰላሙ በቀለ**፣ 2001፣ ***ሕግን እንወቅ*** **(አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ)**

**ኤልያስ ኑር እና ሙራዱ አብዶ** (2007 ዓ.ም፤ እአአ 2015) (**አርታኢዎች**)፣ ***የባሕል ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጵያ*** **ቅጽ** 1 (**አዲስ አበባ፣ የፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት**)

**ጸጋዬ ገብረ መድኅን**፣ 2003፣ ***ታሪካዊ ተውኔቶች፣*** **(አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ)**

# አባሪ፡ ዳሰሳው የመረመራቸው ጽሑፎች
# (Annex፡ List of literature covered in the review)

**የተዳሰሱትን የምርምር ጽሑፎች አንባቢያን መመልከት ይችሉ ዘንድ ይህ ጽሑፍ በጠቅላላው በዋቢነት የመረመራቸው 113 (አንድ መቶ አሥራ ሦስት) ጽሁፎች በአባሪነት ከዚህ በታች ቀርበዋል**


Abdulfetah Abdelah, 2011, "The Customary Legal Institutions of Welene People" (Addis Ababa, Ethiopia)

Abebaw Abebe and Flintan, Fiona, 2021, *Women's land rights: Customary rules and formal laws in the pastoral areas of Ethiopia – complementary or in conflict?* Rangelands Research Report 4 Nairobi, Kenya: ILRI

Aberra Degefa, 2013, "Legal Pluralism in Multicultural Setting: Legal Appraisal of Ethiopia`s Monist Criminal Justice System" in Elias Stebek and Muradu Abdo (eds), *Law and Development, and Legal Pluralism Law and Development Series* No. 1, (Addis Ababa: Justice and Legal Systems Research Institute)

Aberra Jembere, 1992, "*Yatatayaq Muget*: The Traditional Ethiopian Mode of Litigation" *Journal of Ethiopian Law*, vol. 15

Aberra Jembere, 1998, "Legal History of Ethiopia 1434-1974: Some Aspects of Substantive and Procedural Laws"

Aberra Jembere, 2012, *An introduction to the legal history of Ethiopia: 1434–1974*, Addis Ababa, Master Printing Press

Ajanaw Alemie, 2018, "Roles of Indigenous Conflict Resolution Mechanisms for Maintaining Social Solidarity and Strengthening Communities in Alefa District, North West of Ethiopia", *Journal of Indigenous Social Development*, 7 (2)

Aklilu Wolde Amanuel, 1973, "The Fallacies of Family Arbitration under the 1960 Ethiopian Civil Code", *Eth. J. L.*, 9 (1)

Alemayehu Fentaw, 2014 "Legal Pluralism: Its Promises and Pitfalls for Ethiopia", *Jimma University Journal of Law* 1 (1)

Alula Pankhurst and Getachew Assefa (eds), 2008, *Grass-roots Justice in Ethiopia: The Contributions of Customary Dispute Resolution.* Addis Ababa: Centre Français des Etudes Ethiopiennes

Assefa Fiseha, 2013a, Customary Dispute Resolution Mechanisms and the Rule of Law: Areas of Convergence, Divergence and Implications in Elias N. Stebek and Muradu Abdo (eds) *Law and Development, and Legal Pluralism* Addis Ababa: Justice and Legal Systems Research Institute

Assefa Fiseha, 2014b, Improving Access to Justice through Harmonization of Formal and Customary Dispute Resolution Mechanisms. In Pietro Toggia *et al* (eds) *Access to Justice in Ethiopia: Towards an Inventory of Issues*, Addis Ababa: Addis Ababa University Center for Human Rights

Ayalew Getachew, 2012, "Customary Laws in Ethiopia: A Need for Better Recognition?", Working Paper, Danish Institute of Human Rights

Baker, Bruce, 2013a, "Where Formal and Informal Justice Meet: Ethiopia's Justice Pluralism" *African Society of International and Comparative Law*, 21 (1)

Baker, Bruce, 2013b, "Hybridity in Policing: The Case of Ethiopia," *The Journal of Legal Pluralism and Unofficial Law*, 45 (3)

Beckstrom, John, 1969a, "Divorce in Urban Ethiopia Ten Years after the Civil Code", *Eth. J. L., 6 (1)*

Beckstrom, John, 1973b, "Paternity Actions in Ethiopia Ten Years after the Civil Code", *African Law Studies, vol. 9*

Beckstrom, John, 1973c, "Transplantation of Legal Systems: An Early Report on the Reception of Western Laws in Ethiopia", *AM. J. of Comp. L.* vol. 21

Beckstrom, John, 1974d, "Handicaps of Legal-Social Engineering in a Developing Nation", *Am. J. Comp. L.,* vol. 22

Bililign Mandefro, 1969, "Agricultural Communities and the Civil Code: A Commentary", *Eth. J. L.*, 5(1)

Birhanu Bitew, Asabu Sewenet, & Getachew Fentahun, 2021, "Indigenous governance systems and democracy in Ethiopia: Yejoka Qicha system of the Gurage people" *The International Indigenous Policy Journal,* 12(3)

Brietzke, Paul, 1974a, "Private Law in Ethiopia", *Journal of African Law,* vol. 18

Brietzke, Paul, 1976b, "Land Reform in Revolutionary Ethiopia", *The Journal of Modern African Studies*, 14 (4)

Center for International Forestry Research and World Agroforestry (CIFOR-ICRAF) and International Fund for Agricultural Development, 2021, *Women`s Land Rights in Ethiopia*
https://www.cifor.org/publications/pdf_files/Books/Socio-legal-review-Ethiopia.pdf

Cochrane, Logan *et al*, 2020, "The Rush for Land and Agricultural Investment in Ethiopia: What We Know and What We Are Missing", Land vol. 9 (167)

Cuskelly, Katrina, 2011, *Customs and Constitutions: State Recognition of Customary Law around the World,* IUCN, Bangkok, Thailand

Daniel Alemayehu, 2021, "Multiple Legal Orders in Ethiopia: An Impediment on the Enforcement of Women Rights" *Northwestern Journal of Human Rights* Current Issue, 19(1)

Daniel Behailu Geberamanuel and Gemmeda Amelo Gurero, 2017, "The Enigma of Informal Rural Land Deals in Ethiopia: Evidence from Peri-urban Areas of Hawassa City", *Haramaya Law Review* vol. 6

Daniel Haile, 1973, "Law and Social Change in Africa: Preliminary Look at the Ethiopian Experience", *Eth. J. L.* 9 (2)

David, Rene, 1963a, "A Civil Code for Ethiopia: Considerations on the Codification of the Civil Law in African Countries", *Tul. L. Rev.* 37 (2)

David, Rene, 1967b, "Sources of the Ethiopian Civil Code", *Eth. J. L. 4 (2)*

Dolores, Donovan and Getachew Assefa, 2003, "Homicide in Ethiopia: Human Rights, Federalism, and Legal Pluralism" *American Journal of Comparative Law*, 51(3)

Donovan, Dolores, 2021, Book Review: "Legal pluralism in Ethiopia: actors, challenges and solutions, eds. Susanne Epple and Getachew Assefa, Bielefeld, transcript Verlag, 2020" in *The Journal of Legal Pluralism and Unofficial Law*53 (3)

Dunning, Harrison, 1970a, "Land Reform in Ethiopia: A Case Study in Non-Development", *University of California Law Review*, 18 (2)

Dunning, Harrison, 1986b, "Law and Economic Development in Africa: The Law of Eminent Domain", *Colum. L. Rev.*, vol. 68

Elias Stebek and Muradu Abdo (eds), 2013, *Law and Development, and Legal Pluralism*, *Law and Development Series* No. 1, (Addis Ababa: Justice and Legal Systems Research Institute)

Endalcachew Bayeh, 2015, "The Place of Customary and Religious Laws and Practices in Ethiopia: A Critical Review of the Four Modern Constitutions", *Social Sciences*, 4 (4)

Endalew Lijalem Enyew, 2019, "Ethiopian customary dispute resolution mechanisms: Forms of restorative justice?", *AJCR*, 14 (1)

Fantu Faris *et al*, 2013, "Questioning the 'Regulatory Approach' to Large-Scale Agricultural Land Transfers in Ethiopia: A Legal Pluralistic Perspective", *Journal Law and Development Review*

Fisher, Stanley, 1966, "Some Aspects of Ethiopian Arrest Law: The Eclectic Approach to Codification", *Journal of Ethiopian Law*, 3 (2);Vanderlinden, Jacques (1989)c, "Return to Legal Pluralism: Twenty Years Later," *Journal of Legal Pluralism*, no. 28

Fisher, Stanley (1971)a "Traditional Criminal Procedure in Ethiopia" *The American Journal of Comparative Law*, 19 (4)

Fisher, Stanley, 2014b, "50 Years of Legal Education in Ethiopia: A Memoir" *Journal of Ethiopian Law*, vol. 26

Francesco Cecchi and Mequanint Biset Melesse, 2016, "Formal law and customary change: A lab-in-field experiment in Ethiopia, *Journal of Economic Behavior & Organization*

Gebre Yntiso *et al (eds)*, 2011a, *Customary Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia.* Addis Ababa: The Ethiopian Arbitration and Conciliation Centre

Gebre Yntiso, 2014, "Systematizing Knowledge about Customary Laws in Ethiopia", *Journal of Ethiopian Law*, 26 (2)

Gebreyesus Teklu, 2014, "Popular Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia: Trends, Opportunities, Challenges and Prospects", *AJCR*, 14 (1)

Gebreyesus Yimer and Wim Decock, 2018, "Courts and Traditional Financial Institutions in Ethiopia: Selected Case-Studies on Legal Hybridity", *Journal of Legal Pluralism and Unofficial Law* 50

Gemeda Roba, 2019, "Indigenous mechanisms of preserving sacred natural sites in Guji Oromo, Adoola Reedde and Anna Sorra districts, southern Ethiopia", *Cogent Food and Agriculture*, 5 (1)

Geraghty, Thomas, 1969, "People, Practice, Attitudes and Problems in the Lower Courts of Ethiopia", *Eth. J. L. 6 (1)*

Getachew Assefa, 2011, "Federalism and Legal Pluralism in Ethiopia, Preliminary Observations on their Impacts on the Protection of Human Rights", East African Journal of Peace and Human Rights, 17(1)

Girma Selassie, 2007, "Some Nostalgic Thoughts on the Teaching of Law in Ethiopia" *Mizan Law review* 1(1)

Girmachew Alemu, 2015a, "Legal and judicial plurality and the incorporation of traditional dispute resolution mechanisms within the state justice system" in *Non-state justice institutions and the law*

*Girmachew Alemu*, 2020b, "Introduction to the Ethiopian Legal System and Legal Research", https://www.nyulawglobal.org/globalex/Ethiopia1.html

Hailegabriel Feyissa, 2017, "The Ethiopian Civil Code Project: Reading A 'Landmark' Legal Transfer Case Differently", PhD Thesis, Melbourne University, School of Law, https://rest.neptune-prod.its.unimelb.edu.au/server/api/core/bitstreams/df3a12a8-857e-5f76-b854-590955dd4a97/content, accessed August 12, 2022

Heron, Cyril, 2018, "A Christian Oasis: The Role of Christianity and Custom in the Laws of Ethiopia", *Cornell International Law Journal*, 51 (3)

HiiL,2020, "Justice Needs and Satisfaction in Ethiopia: Legal Problems in Daily Life" https://www.hiil.org/wp-content/uploads/2019/09/JNS_Ethiopa_2020-1.pdf

International Commission of Jurists, 2019, "Indigenous and Other Traditional or Customary Justice Systems Selected International Sources", https://www.icj.org/wp-content/uploads/2019/11/Universal-Trad-Custom-Justice-Compil-updated-Publications-2019-ENG.pdf

Kairedin Tezera, 2018, "Dynamics of Identity Formation and Legal Pluralism: the Case of Customary, State and Religious Dispute Resolutions among the Siltie People, Southern Ethiopia", Bayreuth, Germany

Krishnan, Jayanth, 2012, "Academic SAILERS: The F Academic SAILERS: The Ford Foundation and the Efforts to Shape Legal Education in Africa, 1957-1977", *American Journal of Legal History*, vol. 52

Krzczunowicz, George, 1966, "The Law of Filiation under the Civil Code", *Journal of Ethiopian Law*, 3 (2)

Krzczunowicz, George, 1963a, "The Ethiopian Civil Code: Its Usefulness, Relation to Custom and Applicability'', *J.A.* 7(3)

Krzczunowicz, George, 1965b, "Code and Custom in Ethiopia", *Eth. J. L.* 2(2)

Lavers, Tom, 2018, "Responding To Land-Based Conflict in Ethiopia: The Land Rights Of Ethnic Minorities under Federalism" *African Affairs*, 117 (468)

Liku Worku, 2015, "A Critical Ananlysis of Ethiopian Civil Code: In Light of the Core Features of Continental European Codification", L.L.M. Thesis, 2012, School of Advanced Study, University of London

Lowenstein, Steven, 1965, "The Penal System of Ethiopia" *Journal of Ethiopian Law*, 2 (2)

Macfarlane, Julie, 2007, "Working towards Restorative Justice in Ethiopia: Integrating Traditional Conflict Resolution Systems with the Formal Legal System" *Cardozo J. of Conflict Resolution*, 4

*Mattei, Ugo*, 1995, "The New Ethiopian Constitution: First Thoughts on Ethnical Federalism and the Reception of Western Institutions", http://www.jus.unitn.it/CARDOZO/Review/Constitutional/Mattei2.html

Megersa Regassa Tolasa and Dejene Gemechu Chala, 2019, "Oromo Proverbs and Proverbial Expressions in the Customary Judicial System in Ethiopia", *Journal of Ethinology and Folklositics* 13(2)

Mekonnen Firew Ayano, 2018, "Rural Land Registration in Ethiopia: Myths and Realities", *Law and Society Review*, 52(4)

Mengesha Robso Wodajo, 2022, "Women and Land Rights in Western Shoa: In Case of Dano Woreda, 1941-1991", *Education Research International*

Meron Zeleke, 2010, "*Ye Shakoch Chilot* (the court of the sheikhs): A traditional institution of Conflict resolution in Oromiya zone of Amhara regional state, Ethiopia", *African Journal on Conflict Resolution*, 10 (1)

Mizanie Abate, 2020, "Rethinking Litigation Grounded Enforcement of Constitutional Rights in Ethiopia", Journal of Ethiopian Law, vol. 32

Mohammed Abdo, 2011, "Legal Pluralism, Sharia Courts, and Constitutional Issues in Ethiopia", *Mizan Law Review*, 5(1)

Mohammed Abdo, 2020, "Federal Sharia Courts in Addis Ababa their administration and the application of law in the light of recent developments" in Epple, Sussane & Getachew Assefa (eds) *Legal Pluralism in Ethiopia: Actors, Challenges and Solutions* Bielefeld: transcript Verlag

Mohammud Abdulahi, 2007, "Legal Status of the Communal Land Holding System in Ethiopia: The Case of Pastoral Communities", *International Journal on Minority and Groups Rights*, vol. 14

Muradu Abdo, 2008, Book Review: Alula Pankhrust and Getachew Assefa (eds), Grassroots Justice in Ethiopia, The Contribution of Customary Dispute Resolution, *Journal of Ethiopian Law,* vol. 23

Muradu Abdo, 2020, "Compulsory Loss of Pastoral Land Tenure Systems in Ethiopia" (2020) in ES Nwauche (ed*) Citizenship and Customary Law in Africa*

Nesbitt-Ahmed, Zahrah and MacLean, Laura, 2017, "Business Environment Reform Facility Scoping Study on Customary Law and Women's Entrepreneurship", UK Department for International Development

Nigatu Bekele, 2021, "The Legal Status of Communal Land Tenure System in Ethiopia and Its Congruency with the FDRE Constitution" *Oromia Law Journal*, 10(1)

Paul, Benjamin, 1955, *Health, Culture and Community: Case Studies of Public Reactions to Health Programs* (New York: Russel Sage Foundations)

Rakeb Messele Aberra, 2013, "Reflections on Gender Justice and Legal Pluralism" i*n* Elias Stebek and Muradu Abdo (eds) *Law and Development, and Legal Pluralism in Ethiopia, Justice and Legal System Research Indtitute*

Rakeb Messele Aberra, 2013, "Reflections on Gender Justice and Legal Pluralism" in Elias Stebek and Muradu Abdo (eds) *Law and Development, and Legal Pluralism in Ethiopia*

Samuel Yohanis Degoma Tegbaru Terefe Feyissa, 2010, "Community Participation as Power Distribution: Insight into Law and Practice in Sheka Forests Conservation", *Mizan Law Review,* 15(2)

Scott, James, 1998, *Seeing Like A State: How Certain Schemes to Improve the Human Condition Have Failed*, (New Haven and London, Yale University Press)

Selamu Bekele, 2007, "Living with My Strange Thoughts", *Mizan Law review* 1(1)

SIHA Network Strategic Initiative for Women in the Horn of Africa, 2011, "Building Universality from Below: A Project on Customary Laws and Practices which Impede Access to Rights for Women and Girls in Oromia, Ethiopia".

Singer, Norman, 1970c, "Modernization of Law in Ethiopia: A Study in Process and Personal Values", *11 Harv. Int`l. L. J.* 73

Singer, Norman, 1970-1971a, "A Traditional Legal Institution in a Modern Legal Setting: The Atbia Dagnia of Ethiopia" *UCLA L. Rev.*, 18

Singer, Norman, 1971-1973b, "Islamic Law and the Development of the Ethiopian Legal System" *Howard L. J.* 17

Singer, Norman, 2008d, "The Early Days of the Faculty of Law, AAU", *Mizan Law Review,* 2:1

Singer, Norman, 2008e, "Three Eye-opening Events", *Mizan Law Review*, 2(2)

Singer, Norman, 1971-1972f, "The Ethiopian Civil Code and the Recognition of Customary Law", *Hous. L. Rev., vol 9*

Stellmacher, Till, 2013, Local forest governance in Ethiopia: Between legal pluralism and livelihood realities, ZEF Working Paper Series, No. 110, University of Bonn, Center for Development Research (ZEF), Bonn

Strauss, Peter, 2009, "To and From the Community", *Mizan Law review* 3(1)

Susanne Epple and Getachew Assefa (eds), 2020 *Negotiating Law in the Peripheries of Southern Ethiopia*, Columbia Universioty Press

Toggia, Pietro *et al* (eds), 2014, *Access to Justice in Ethiopia: Towards an Inventory of Issues* Addis Ababa University, Center for Human Rights

Tsegai Berhane Ghebretekle and Macdonald Rammala, 2018, "Traditional African Conflict Resolution: The Case of South Africa and Ethiopia" *Mizan Law review* 12 (2)

Tsegai Berhane Ghebretekle, 2017, "Traditional natural resource conflict resolution vis-à-vis formal legal systems in East Africa: The cases of Ethiopia and Kenya", https://reliefweb.int/report/ethiopia/traditional-natural-resource-conflict-resolution-vis-vis-formal-legal-systems-east

Tsegaye Beru, 2019, "Brief History of the Ethiopian Legal Systems - Past and Present", *International Journal of Legal Information,* 41(3)

Tsehai Wada, 2012, "Coexistence between the Formal and Informal Justice Systems in Ethiopia: Challenges and Prospects" *African Journal of Legal Studies*, 5.

Tuori, Kaius, 2010, "Legal Pluralism and Modernization: American Law Professors in Ethiopia and the Downfall of the Restatements of African Customary Law", *Journal of Legal Pluralism,* No 62

Vanderlinden, Jacques, 1966a, "An Introduction to the Sources of Ethiopian Law from the 13th to the 20th Century", *Eth. J. L.* 3 (1)

Vanderlinden, Jacques, 1966b, "Civil Law and Common Law Influences on Developing Law of Ethiopia", *Buffalo L. Rev.,* vol. 16

Vanderlinden, Jacques, 1966d, "A Further Note on an Introduction to the Sources of Ethiopian Law", *Eth. J. L.*, vol.3

Wondimagegene Gebre, 2014, “The Role of Traditional and Informal Justice in Promoting Access to Criminal Justice: A Comparative Study” in Pietro Toggia (eds.) *Access to Justice in Ethiopia: Towards an Inventory of Issues* (Addis Ababa University)

Wondwossen Demissie and Muradu Abdo, 2017, “Legal Status of Customary Criminal Justice Systems and Human Rights in Ethiopia” in Weber, Leanne *et al* (eds) The Routledge International Handbook of Criminology and Human Rights

Yedenekachew *et al*, 2013, “Case Study on Seven Customary Laws in Ethiopia” (in Gebre Yntiso*et al* (eds), 2012b *Customary Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia.* Addis Ababa: The Ethiopian Arbitration and Conciliation Center

Yonas Birmeta (ed) “Human Rights and Legal Pluralism in Ethiopia” *Ethiopian Human Rights Law Series*, vol 7 (?)

Yonatan Fesseha, 2013, “Pluralism and the South African Experience: Customary Law as a Constitutional Right” in Elias Stebek and Muradu Abdo (eds) *Law and Development, and Legal Pluralism in Ethiopia* (

Zaki Mustfa, 1973, “The Substantive Law Applied by Muslim Courts in Ethiopia”, *Journal of Ethiopian Law*, 9 (1)

ሰላሙ በቀለ፣ 2001፣ *ሕግን እንወቅ* (አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ)

ኤልያስ ኑር እና ሙራዱ አብዶ (2007 ዓ.ም፤ እአአ 2015) (አርታኢዎች)፣ *የባሕል ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጵያ* ቅጽ 1 (አዲስ አበባ፣ የፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት)

ጸጋዬ ገብረ መድኅን፣ 2003፣ *ታሪካዊ ተውኔቶች፣* (አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ)